# ተረበኛው

# ናስሩዲን

## ቀልድ - ቀመስ - ቁምነገሮች

ደራሲ — ኢድሪስ ሻህ

ተርጓሚ — አማረ ማሞ

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት

1981

Ethiopia Book Centre

1988

Original title:
The Exploits of the
Incomparable
Mulla Nasrudin
by Idries Shah
Amharic Adaptation
by Amare Mamo

ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
የፖ. ሣ. ቁ. 1024 አዲስ አበባ

Ethiopia Book Centre
P. O. Box 1024 Addis Ababa

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።

All Rights Reserved

ሠዓሊ - ቦጋለ በላቸው ።

በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ ።
Printed by Artistic Printers

# መግቢያ

ሙላ (አለቃ) ናስሩዲን ዓለም አቀፍ የሥነ—ቃል አፍላቂ ሰው ነበር ። የኖረበት የታሪክ ወቅት በመካከለኛው ዘመን ቢሆንም ፣ ቁም ነገር—ቀመስ—ቀልዶቹ በመረሳትና በመዘንጋት ፋንታ ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሸቱና እየጐለበቱ የሚሔዱና በሚሊዮን የሚቈጠሩ የተለያዩ አገር ሕዝቦችን የሚያዝናኑ ፣ የሚያመራምሩና የሚያወያዩ ከመሆን አላቋረጡም ።

ናስሩዲንን የአገራቸው ዜጋ አድርገው የሚቈጥሩ ሕዝቦች ጥቂት አይደሉም ። ግሪኮች ፣ ግብፃውያን ፣ ኢጣሊያኖች ፣ ቀልዶቹን እንደ ራሳቸው የሥነ—ቃል ቅርስ ይቈጥሩታል ። ራሽያኖች በናስሩዲን ቀልዶች ላይ የተመሠረተ ፊልም በማቀናበር የአገራቸውን የገዥ መደብ አባላት ማጋለጫ አድርገው ተጠቅመውበታል ።

የናስሩዲንን የቈየ ቅርስ «የኛ ነው» የሚለውን እምነታቸውን አጥብቀው በመያዝ ቱርኮችን የሚወዳደር አልተገኘም ። ናስሩዲን በቱርክ አገር ኤክስሼር ከተማ መወለዱን ብቻ ሳይሆን ፣ እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቀን አቆይተናል የሚሉትን መቃብሩን ለዓለም በይፋ በማሳየት ላይ ይገኛሉ ። ከዚህም በቀር ፣ በዓመት አንድ ጊዜ በናስሩዲን ስም የተሠየመ ፌስቲቫል በማዘጋጀት ፣ የሙላ ናስሩዲን ቀልዶች በይፋ እንዲዘከሩ ያደርጋሉ ። ቱርኮች ለአገር ጐብኝዎች ከሚያቀርቧቸው የመረጃ ጽሑፎቻቸው ውስጥ የናስሩዲንን ቀልዶች በመስሕብነት ይጠቀሙባቸዋል ።

ከቀልዶቹ ይዘት እንደምንረዳው ከሆነ ፣ ናስሩ ዲን በሕይወት ዘመኑ ያልረገጠው አገር ፣ ያልሆነው ነገር የለም ። የሕይወትን የተለያዩ ገጽታዎች በመ ዳሰስ ረገድ በእጅጉ ተለዋዋጭ የሆነ ሚና ሲጫወት እናገኘዋለን ። ናስሩዲን ፣ ዛሬ ቂል ፣ ነገ ጠቢብ በተ ለያዩ ጊዜያት ደግሞ ፣ ያገር አስተዳዳሪዎች አማካሪ ፣ ለማኝ ፣ መምህር ፣ ሐኪም ፣ ፈላስፋ ፣ በሽተኛ ሆኖ የመገኘትን ሚና እያፈራረቀ የሚላበስ ሰው እንደነ በረ መረዳት አያዳግትም ። ተረበኛው ናስሩዲን ስለ ራሱ ሲናገር ፣ «እኔ ሕይወቴን ያሳለፍኩት የግልብ ጦሽ ነው» ያለው አለምክንያት አይደለም ።

የናስሩዲን ቀልድ—ቀመስ—ቁምነገሮች ለአ ማርኛ አንባቢዎች ሊጥሙ በሚችል መንገድ ለማቅ ረብ ጥረት ተደርጓል ። በተለይም የአገራችን ሕዝብ የረጅም ዘመናት ገጠመኙ ቅርስ የሆኑትን ምሳሌአዊ አነጋገሮች በተቻለ መጠን ከቀልዶቹ ጋር ለማዋሐድ ተደክሞበታል ።

የናስሩዲንን ቀልዶች የመረመረ አንድ ሐያሲ ፣ «በየዘመናቱ አያሌ ሰዎች ከናስሩዲን ተረቦች ብዙ ጥበብ ፣ ብዙ ምስጢር ፣ ብዙ የፍልስፍና እውነታ ለመቅሰም ጥረት አድርገዋል ። ዛሬ ቀልዶቹን የሚያ ነብ ማንኛውም ሰው — ሌላው ቢቀር — ሁለት ጠቀሜታዎችን እንደሚያገኝባቸው ጥርጥር የለውም። ቀልዶቹን በጥሞና በማንበብ ደስታን ያተርፋል ፤ የሕይወትን ጉራማይሌ ገጽታ ለማገናዘብ ይረዱ ታል» የሚል አስተያየት ሰንዝሮአል ።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ዓላማም ይኸው ነው ።

አማረ ማሞ ።

ከቀልዶቹ ይዘት እንደምንረዳው ከሆነ ፥ ናስሩዲን በሕይወት ዘመኑ ያልረገጠው አገር ፥ ያልሆነው ነገር የለም ። የሕይወትን የተለያዩ ገጽታዎች በመዳሰስ ረገድ በእጅጉ ተስዋዋጭ የሆነ ሚና ሲጫወት እናገኘዋለን ። ናስሩዲን ፥ ዛሬ ቂል ፥ ነገ ጠቢብ በተለያዩ ጊዜያት ደግሞ ፥ ያገር አስተዳዳሪዎች አማካሪ ፥ ለማኝ ፥ መምህር ፥ ሐኪም ፥ ፈላስፋ ፥ በሽተኛ ሆኖ የመገኘትን ሚና እያፈራረቀ የሚላበስ ሰው እንደነበረ መረዳት አያዳግትም ። ተረበኛው ናስሩዲን ስለ ራሱ ሲናገር ፥ «እኔ ሕይወቴን ያሳለፍኩት የግልብ ጦሽ ነው» ያለው አለምክንያት አይደለም ።

የናስሩዲን ቀልድ—ቀመስ—ቁምነገሮች ለአማርኛ አንባቢዎች ሊጥሙ በሚችል መንገድ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል ። በተለይም የአገራችን ሕዝብ የረጅም ዘመናት ገጠመኙ ቅርስ የሆኑትን ምሳሌአዊ አነጋገሮች በተቻለ መጠን ከቀልዶቹ ጋር ለማዋሐድ ተደክሞበታል ።

የናስሩዲንን ቀልዶች የመረመረ አንድ ሐያሲ ፥ «በየዘመናቱ አያሌ ሰዎች ከናስሩዲን ተረቦች ብዙ ጥበብ ፥ ብዙ ምስጢር ፥ ብዙ የፍልስፍና እውነታ ለመቅሰም ጥረት አድርገዋል ። ዛሬ ቀልዶቹን የሚያነብ ማንኛውም ሰው — ሌላው ቢቀር — ሁለት ጠቀሜታዎችን እንደሚያገኝባቸው ጥርጥር የለውም። ቀልዶቹን በጥሞና በማንበብ ደስታን ያተርፋል ፤ የሕይወትን ጉራማይሌ ገጽታ ለማገናዘብ ይረዱታል» የሚል አስተያየት ሰንዝሮአል ።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ዓላማም ይኸው ነው ።

አማረ ማሞ ።

# ስድቡኝ ባይ

ናስሩዲን ከአንድ የታወቀ ፈላስፋ ጋር በአንድ ርዕስ ላይ ክርክር ለመግጠም ተቃጥረው ፥ ፈላስፋው በቀጠሮው ቀንና ሰዓት ናስሩዲን ቤት ቢሔድ ፥ ቤት አለመኖሩ ተነገረው ። ፈላስፋው ናስሩዲን ቀጥሮት በመጥፋቱ በጣም ተበሳጨ ። ከብስጭቱ ብዛት የተነሣ ፥ የናስሩዲንን በር በርግዶ ከወጣ በኋላ ፥ መዝጊያው ላይ ፥ «ደደብ !» የሚል ቃል በጉልሕ ጽፎ ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

ናስሩዲን ከሔደበት ሲመለስ በሩ ላይ የተጻፈውን ቃል አየ ። ቤቱ ገብቶ ብዙም ሳይቆይ ወደ ፈላስፋው ቤት አመራ ። እዚያም እንደ ደረሰ ፈላስፋውን እንዲህ አለው ፡—

«ቀጠሮ እንደ ነበረን እርስት ነው ያደረግሁት ። የመጣሁትም ከልብ ይቅርታ ለመጠየቅ ነው ። ከሔድኩበት ስፍራ ስመለስ በሬ ላይ ያስፈርከውን ፊርማህን በማየቴ ነው ቀጠሮአችን ትዝ ያለኝ !»

— ስድቡኝ ባይ አመንገድ ዳር ይጸዳዳል ።

# ውሻ በላው

ናስሩዲን እንግዶችን ለመጋበዝ በማሰብ ሦስት ኪሎ ሥጋ ገዝቶ አስፈላጊውን እንድታዘጋጅ ለሚስቱ ሰጣት ። የተጠሩት እንግዶች መጥተው ምግቡ ሲቀርብ ፣ አንዳችም ሥጋ የሌለበት አሸር ባሸር ምግብ መሆኑ ናስሩዲንን አሳፈረው ። ቢቸግረው ፣ «ምነው ሥጋ አልነበረም እንዴ ?» በማለት ባለቤቱን በለዘብታ በእንግዶቹ ፊት ጠየቃት ።

ሚስቱም ፣ «ሦስቱንም ኪሎ ድመቷ እንክት አድርጋ በላችው!» ስትል ድርቅ ብላ መለሰች ።

ናስሩዲን ለሚስቱ ምንም መልስ ሳይሰጥ ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ተነሥቶ ከሔደ በኋላ ፣ ድመቷን ከአንድ ሚዛን ጋር ይዟት ከተፍ አለ ። እንግዶቹ ፊት ሚዛኑን አስቀምጦ ድመቷን እላዩ ላይ ቁጭ አደረጋት ። ልክ ሦስት ኪሎ መዘነች ።

ናስሩዲን ፣ የሚዛኑን ምላስ ሚስቱ እንድታይ እያመለከተ ፣ «ሚዛኑ ላይ ያለችው ድመቷ ከሆነች ሥጋው የት ገባ ? የተመዘነው ሥጋው ከሆነ ደግሞ ፣ ድመቷ የት ደረሰች ?» አላት ።

— ውሻም በላው አንቺም በላሽው ካልከደንሽው ።



# የለመደች ጦጣ

አንድ ቀን ናስሩዲን አህያውን ጨው ጥርቅም አድርጎ ጭኖ ገበያ ወጣ ። በመንገዱ ላይ የነበረው ወንዝ ሞላ ብሎ ስላጋጠመው ሰፋ ያለ መልካ ፈልጎ አህያውን እየጐተተ ለመሻገር ወንዝ ውስጥ ገባ ። ወንዙ መሐል እንደ ደረሰ ፥ አህያ ሆዬ እግሮቹን ወንዙ ውስጥ ተክሎ አልነቃነቅም አለ ። ናስሩዲን በመናደድ በያዘው ሽመል አህያውን ይነርተው ጀመር ። አህያው ዱላ ሲበዛበት እየወደቀና እየተነሣ ወንዙን ተሻገሩ ። ጨዉ ወንዙ ውስጥ ሟምቶ በመገባደዱ አህያው ሸህሙ ስለቀለለው መንገዱን በፍጥነት ማቀላጠፉን ተያያዘው ።

በሌላ ጊዜ ናስሩዲን ያንኑ አህያ ጭኖ ገበያ ሲወጣ ከወንዙ ደረሰ ። ናስሩዲን አህያውን እየጐተተ ወንዙ ውስጥ ገባ ። መሐል እንደ ደረሱ አህያው አሁንም ግትር ብሎ በመቆም ጭነቱን ወራጅ ውኃ ያስመታ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን አህያውን አልመታውም ። ለጥቂት ጊዜ አጠገቡ ዝም ብሎ ከቆመ በኋላ ፥ መሳቢያውን ገመድ ጐተት ጐተት አደረገው ። አህያውም እንደ ምንም ብሎ ወንዙን ተሻገረ ። መንገዳቸውን ሊጀምሩ ሲሉ ከጭነቱ ክብ ደት የተነሣ የአህያው ወገብ ተለምጦ መሬት ሊነካ ደረሰ ።

ናስሩዲንም አህያውን ፥ «የኛ ብልጥ ! ወንዝ አቋርጠህ ባለፍህ ቍጥር እንደ ለመድከው የጭነትህ ክብደት የሚቃለልልህ መስሎህ ነበር ። ዛሬ ጨው ሳይሆን ጥጥ ነው የተጫንከው !» አለው ።

— የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ ።



# ኮንትሮባንዲስቱ

ናስሩዲን ለብዙ ዘመናት አህዮች እየያዘ ከፋርስ ወደ ግሪክ አገር ይመላለስ ነበር ። አህዮቹን ድርቆሽ ጭኖ የግሪክ አገር ኬላ ጠባቂዎች ዘንድ ሲቀርብ ፣ ጠባቂዎቹ ድርቆሹንም እርሱንም በሚገባ ሲፈትሹ ምንም የሚቀረጥ ዕቃ ስለማያገኙበት እንዲያልፍ ይፈቅዱለታል ።

አንድ ጊዜ ናስሩዲን ተፈትሾ ካበቃ በኋላ ፣ ከኬላ ጠባቂዎቹ አንዱ ፣ «ለመሆኑ አንተ በምን ሥራ ነው አገራችን እንዲህ የምትመላለሰው ?» በማለት ጥያቄ ያቀርብለታል ። ናስረዲን ምንም ሳያመነታ ፣« ኮንትሮባንድ እነግዳለሁ» ብሎ ይመልሳል ። ኬላ ጠባቂው የናስሩዲንን መልስ በቀልድ መልክ ይመለከተውና ዝም ይለዋል ።

ብዙ ዓመት ካለፈ በኋላ የግሪክ ኬላ ጠባቂዎች አለቃ ናስሩዲንን ግብፅ አገር ከታወቁ ሀብታሞች ጋር ሲዝናና ያገኘዋል ። አብረው ሲጫወቱ ከቆዩ በኋላ ፣ የግሪኩ የኬላ ጠባቂዎች አለቃ ናስሩዲንን እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል ፡—

«ወዳጄ ናስሩዲን ፤ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ ፤ መቼም አሁን ያለኸው የግሪክ መንግሥት በማያዝበት አገር በመሆኑ እውነቱን ሳትደብቅ እንደምትነግረኝ አምናለሁ ። እንደማይህ በቂ ሀብት ያለው ሰው ትመስላለህ ። ያኔ አገራችን ስትገባና ስትወጣ የኮንትሮባንድ ዕቃ እናገኝብህና እንይዝሃለን በማለት ጥረት አድርገን አልተሳካልንም ። ለመሆኑ አገራችን እየያዝህ ትገባ የነበረው 'የኮንትሮባንድ ዕቃ' ምን ነበር ?»



ናስሩዲን ኩት ብሎ እየሣቀ ፥ «መቼም ያለፈው አልፋል ፤ እኔም የተቻለኝ ጌታ ለመሆን ስለ በቃሁና ወደዚያም ሥራ ስለማልመለስበት ምስጢሬን ብገልጽልህ ምንም አይደለም ። ይኸውልህ ፥ ያኔ አገራችሁ ይገቤ እገባ የነበረው የኮንትሮባንድ ዕቃ አህዮችን ነበር» አለው ።

## ፍርድ ከራስ

ጠቢባን ፥ ፈላስፎች ፥ የሕግና የሃይማኖት ሊቃውንት በተሰበሰቡበት ችሎት ፊት ናስሩዲን ተከሰ ይቀርባል ። የተከሰሰበት ወንጀል ፥ «በየመንደሩ እየዞረ ፥ አዋቂዎች ፥ ጠቢባንና የሃይማኖት መምህራን እንዳች የዕውቀት ቅንጣት በአዕምሮዎቻቸው ውስጥ ያልተቀረጸ ፥ አላዋቂዎችና ደንቆሮዎች ስለሆኑ እነርሱን አትስሙ ፤ እነርሱ በሚሏችሁ አትመሩ» እያለ ሕዝቡን አወናብዷል የሚል ነበር ።

ናስሩዲን ዳኛው ፊት ከቀረበ በኋላ ፥ ለቀረበበት ክስ የሚሰጠው መልስ እንዳለው ይጠየቃል ።

«ወረቀትና እርሳሶች ይቅረቡልኝ» ይላል ናስሩዲን ። በርከት ያለ ወረቀትና እርሳሶች ከቀረቡለት በኋላ ፥ «እፊት ለፊት ለተቀመጡት ሰባት ምሁራን አንዳንድ ገጽ ወረቀትና አንዳንድ እርሳስ ይታደልልኝ ይላል — ናስሩዲን ። የጠየቀው እንዲፈጸም ዳኛው ያዛሉ ።

«ዳቦ ምንድን ነው ? ለሚለው ጥያቄ ፥ እያንዳንዱ ምሁር መልሱን በተሰጠው ወረቀት ላይ ያስፍር» ይላል ናስሩዲን ። ሰባቱም ምሁራን የጥያቄውን መልስ በተሰጣቸው ወረቀት ላይ ያሰፍራሉ ።

መልሶቹን የያዙት ወረቀቶች ተሰብስበው ለዳኛው እንዲቀርቡና ዳኛውም መልሶቹን ቢይፉ ለተ

ሰበሰበው ተመልካች እንዲያነቡ ናስሩዲን በትሕትና ይጠይቃል ።

ዳኛው ጥያቄውን ይቀበላሉ ።

መጀመሪያ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ የሰው ምግብ ነው ።»

ሁለተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ የዱቄትና የውኃ ውሕደት ነው ።»

ሦስተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ የፈጣሪ በረከት ነው ።»

አራተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ እሳት የገባው ሊጥ ነው ።»

አምስተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ እንዳነጋገሩ ፈሊጥና ዘይቤ ብዙ ተለዋዋጭ ትርጒም ሊሰጠው የሚችል ቃል ነው ።»

ስድስተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ የምግብነት ባሕርይ ጐልቶ የሚታይበት ነገር ነው ።»

ሰባተኛ መልስ ፣ «ዳቦ ፣ በዚህ ወይም በዚያ ትርጒም ሊወሰን ይችላል የሚል ብያኔ ሊሰጠው የማይችል ነገር ነው ።»

ናስሩዲን ሰባቱ ጠቢባን የሰጡትን መልስ በጥሞና ካዳመጠ በኋላ ፣ የሚከተለውን ቃል ለዳኛው አሰማ ፤ «ክቡር ሆይ ፤ እስቲ እንግዲህ እርስዎ ይፍረዱኝ ! ብይፉ እንደ ሰማነው ሰባቱም ጠቢባን ፣ በየዕለቱ በእጃቸው እየቈረሱ ፣ በአፋቸው እየጐረሱ ለሚመገቡት ዳቦ ፣ ሰባት ዓይነት ትርጒም ነው የሰጡት ። እንግዲህ ፣ እነዚሁ ጠቢባን ናቸው ወንጀለኛ ብለው ከሰሰው ፍርድ ፊት እንድቀርብ ያደረጉኝ ። ለመሆኑ የእነዚህን ሰዎች ቃል ማመን ፣ እነርሱ ያቀረቡትን ክስ መሰረት አድርጎ ትክክለኛ ፍርድ መበየን እንዴት ይቻላል ? ክቡር ሆይ ፤ ፍርድ ከራስ ነውና እርስዎ ይፍረዱኝ !»

— ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል ።

# ነገር በነገር ይጠቀሳል

ናስሩዲን የሚኖርበት አገር ንጉሥ ባለሟሎቹን ሰብስቦ ፣ ከአገሬው ሕዝብ መካከል በጨዋነቱ የታወቀ ሰው ተፈልጎ እንዲቀርብለትና የዳኝነት ሹመት ሊሰጠው እንዳሰበ ያስታውቃቸዋል ። የንጉሡን ትእዛዝ የሚያስፈጽም አንድ የመልእክተኞች ቡድን ይሠየምና በአገሩ ውስጥ እየተዘዋወረ መስፈርቱን የሚያሟላ ተስማሚ ሰው ለማግኘት ሥራውን ይጀምራል ። የንጉሡ ፍላጐት ወሬም ከናስሩዲን ጆሮ ይደርሳል ።

ናስሩዲን ከሚኖርባት ከተማ ነዋሪዎች መካከል የንጉሡ መልእክተኞች እንዲያነጋግሯቸው ከተመረጡት ሰዎች መካከል እርሱ አንዱ ይሆናል ። ናስሩዲን ፣ በተያዘለት ቀን ቀጠሮ ፣ ከለበሰው ልብስ ላይ የዓሣ ማጥመጃ መረብ ደርቦ መልእክተኞቹ ፊት ይቀርባል ።

በናስሩዲን አለባበስ የተገረመው የመልእክተኞች መሪ ፣ «እስከ ዛሬ በያለበት ስንዘዋወር እንዳንተ የለበሰ ሰው ፈጽሞ አላጋጠመንም ። በልብስህ ላይ የዓሣ ማጥመጃ መረብ የደረብክበት ምክንያት ምንድን ነው ?» በማለት ይጠይቀዋል ።

«ከሥር ከመሠረቴ ድሃ የድሃ ልጅ በመሆኔ ፣ መተዳደሪያዬም ዓሣ ማጥመድ ነበር ። ይህንን መረብ ዘወትር በልብሴ ላይ የምደርበው ያንን የድሮ ኑሮዬን እንዳልዘነጋ በማለት ነው» ሲል ናስሩዲን ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ይሰጣል ።

መልእክተኞቹ ተልእኮአቸውን ፈጽመው ለንጉሡ ባቀረቡት ሪፖርት የናስሩዲን ስም ከሁሉ ጐልቶ ይታያል ።

ንጉሡም ስለ ናስሩዲን የቀረበውን ዘገባ በመ ቀበል የዳኝነቱን ሹመት ይሰጠዋል ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ፣ ምርጫውን ካካሄዱት ባለ ሥልጣኖች አንዱ ፣ ናስሩዲን በታላቅ ችሎት ላይ ተሠይሞ አቤቱታ ሲሰማ ፣ የፍርድ ብያኔ ሲሰጥ ፣ ለተበደለው ሲፈርድና በደለኛውን ሲቀጣ ያገኘዋል ። ከችሎት መልስ ፣ ናስሩዲንና ባለሥልጣኑ ጥቂት ሲጫዋወቱ ከቆዩ በኋላ ፥—

«ያን መረብህን ምነው ዛሬ አላየሁትም ?» በማለት ይጠይቀዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «የምን መረብ ነው ደግሞ ! ዓሣው ከተያዘ በኋላ መረቡ ምን ይፈይዳል ?» በማለት ይመ ልሳል ።

— ነገር በነገር ይጠቀሳል ፤ እሾህ በእሾህ ይነቀሳል ።

## በሰፈሩት ቁና

ናስሩዲን አንድ የደለበ ሙክት ነበረው ። ወዳጅ ዘመዶቹና ጐረቤቶቹ ፣ «እባክህን ይህንን ሙክት እረድና አንድ ቀን እንንበሸበሽበት» እያሉ ቢወተ ውቱም ናስረዲን አልበገር ብሎ አስቸገረ ። ሙክቱን ለመብላት የቋመጡት የናስሩዲን ወዳጆችና ጐረቤ ቶች ፣ የተስማሙበትን መላ ይዘው አንድ ቀን ወደ ናስሩዲን በመቅረብ ፣ «ይኸውልህ ናስሩዲን ፤ ከሦ ስት ቀን በኋላ የዓለም ፍጻሜ ሊሆን ነው ። ሌላው ነገር ሁሉ ይቅር ግድ የለም ። ይህንን ሙክትህን ለመ ብላት እንደተመኘን እንዴት እንቅር ?» ይሉታል ።

ናስሩዲንም በነገሩ በመስማማት ፣ ለዓለም ፍጻሜ ዋዜማ ሙክቱን አርዶ ድል ያለ ድግስ እንደ ሚያበላቸውና ታዳሚዎች በሙሉ እሱ ቤት እንዲ ያድሩ ተስማምተው ይለያያሉ ።

የዓለም ፍጻሜ ይሆናል በተባለበት ዋዜማ ምሽት ፣ ምግቡም መጠጡም እንደ ልብ ተዘጋጅቶ እንግዶቹም እስኪበቃቸው ድረስ በልተው ጠጥተው ካበቁ በኋላ ፣ ሁሉም የላይ መደረቢያ ልብሶቻቸውን እያወላለቁ ባገኙበት ቦታ ፍንግል አሉ ። ናስሩዲንም እንግዶቹ አውልቀው ያስቀመጡትን ልብሶች በሙሉ ሰብስቦ ፣ አንድ ቦታ በመከመር በጧፍ ያቀጣጥልና የሚንቦገቦገውን እሳት ሲሞቅ ያድራል ። ሰዎቹ ከእ ንቅልፋቸው ሲነቁ ልብሶቻቸው ለእሳት ተዳርገው በማግኘታቸው ጩኸትና ውካታ በመፍጠር ናስሩ ዲንን ያዋክቡታል ።

ናስሩዲንም በእርጋታ ፣ «ወዳጆቼ ፤ እንዲህ አድርጎ በመጮህና ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ሥርዓት ማጣት ደግ አይደለም ። እስቲ ነገሩን በእርጋታ ተመ ልከቱት ። እናንተው እንደ ነገራችሁኝ ከጥቂት ሰዓ ታት በኋላ የዓለም ፍጻሜ ይሆናል ። በዚያን ጊዜ ማቄን ጨርቄን ማለት አይኖርም ። የዓለምን ፍጻሜ ዋዜማ ድል ባለው ድግሴ ማክበራችሁን ረሳችሁት እንዴ ?» አላቸው— ፈገግ እያለ ።

— በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም ።



# ይሉሽን በሰማሽ

የናስሩዲን ሠርግ የሚበላበት ዕለት ነበር ። በአገሩ ባህል መሠረት ፥ ናስሩዲን የሚያገባትን ሴት ቀደም ብሎ የማየት ዕድል አላጋጠመውም ነበር ። የጋብቻው ዕለት የሙሽሪት ፊት በዓይነርግብ መሸፈን ነበረበት ። የጋብቻው ሥነ—ሥርዓት ተፈጽሞ እንዳበቃ ፥ ሙሽሪት ዓይነርግብዋን ገልጦ ፥ ፊትዋን ወደ ባልዋ መለስ ስታደርገው ፥ ናስሩዲን ያገባት ሴት በመልክ ጥፉነትዋ የምታስፈራ ሆና አገኛት ።

ዕድሉን እያማረረ በሐሳብ ሲባዝን ሳለ ፥ ሙሽሪት ከወደ ጎኑ ጐንተል ታደርገውና ፥ «ፍቅርዬ ፤ ባል እንግዲህ ትእዛዝህን ልስማው ፤ ፈቃድህን ልወቀው ። ከሁሉ በፊት በእነማን ዘንድ ፊቴን መሸፈን በነማንስ ፊት መስከንተሪያዬን ገልጬ ፊቴን ማሳየት እንዳለብኝ ንገረኝ» አለችው ።

ናስሩዲንም ፥ «የኔ እመቤት ፤ ፊትሽን ለፈለግሽው አላፊ አግዳሚ ገልጠሽ ማሳየት ትችያለሽ ። ከእኔ ጋር ስትሆኚ ግን ፥ ሁለት ሦስት ዓይነርግብ ደራርበሽ ተሸፋፈኚ !» አላት ፥ ተስፋ በቈረጠ ስሜት ።

— ይሉሽን በሰማሽ ፥ ገቢያ ባልወጣሽ ።

# የወደዱትን ቢያጡ

ናስሩዲን በሕልሙ አንድ ሰው ገንዘብ እየቈጠረ ሲሰጠው ያያል ። ቍጥሩ ዘጠኝ ላይ ሲደርስ ሰውዬው ገንዘብ መስጠቱን ያቆማል ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ይናደድና ፥ «ከሰጠኸኝ አይቀር አሥር ሙላልኝ ! ይህን ጐደሎ ቍጥር እኔ አልወስድም !» ብሎ ይጮሃል ። የገዛ ጩኸቱ ናስሩዲንን ከእንቅልፉ ይቀሰቅሰዋል ።

ዓይኑን ገልጦ ቢመለከት ፥ ቤሳቤስቲን እጁ ውስጥ እንደ ሌለ ይመለከታል ። ወዲያው መልሶ ዓይኖቹን ክድን ያደርግና ፥ «አሥር ካልሞላህልኝ በማለቴ አጥፍቻለሁ ። የሆነው ይሁን ፤ ዘጠኙንም ቢሆን ስጠኝ !» አለ ።

— የወደዱትን ቢያጡ ፥ የጠሉትን ይቀላውጡ ።

# ተመልሶ ለራሴ

ናስሩዲን ሚስቱን በሆነባልሆነው ነገር ያበሳጫታል ። አንድ ቀን ለራቱ ሾርባ ትሠራለትና ትናጋውን እንዲያነደው በማቀድ እስቲንተከተክ አፍልታ ታቀርብለታለች ። ባልዋ ከሾርባው ፉት ብሎ ሲቃጠል ለማየት አቆብቁባ ሳለች ፣ ለራስዋ ያቀረበችው ሾርባ ትኩስ መሆኑን በመዘንጋት ፣ ጨለፍ አድርጋ ብትውጠው ፣ አንጀትዋን እርር ድብን ያደርጋታል ። ዕንባዋም ዱብ ዱብ ማለት ይጀምራል ።

ናስሩዲን ፣ «ምነው ምን ነካቶሽ ነው የምታለቅሺው ?» ይላታል ።

«እረ ምንም አልነካኝ ! እንዲያው እናቴ ትዝ ብላኝ ነው ። የሞተች ዕለት ይህንን የመሰለ ሾርባ ነበር አብረን የበላነው ። ትዝታዋን ቀስቅሶብኝ ነው የማለቅሰው» በማለት ትመልስለታለች ።

ናስሩዲንም ከሾርባው ጨለፍ አድርጎ ፉት ሲልለት ፣ ግለቱ ከተቀመጠበት አስፈንጥሮ አስነሣው ። እንባው በጉንጮቹ ላይ ኮለል እያለ መውረድ ጀመረ ።

«ምነው ምን ነካህ ? አንተ ደግሞ ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው ?» ትለዋለች— ሚስቱ ።

«እኔ . . . እኔ እንኳን . እኔ የማለቅሰው . . . እናትሽ አንቺን እዚህ ዓለም ላይ ጥለው በመሞታቸው ነው !» አላት ።

— የወረወርኩት እንካሴ ተመልሶ ለራሴ ።



# አህያ ሠባ

ናስሩዲን ገበያ ወጥቶ አንድ ወደል አህያ ይገዛል ። አህያውን የሸጠለት ሰውዬ ንብረቱን ገበያ አውጥቶ ሊሸጥ የተገደደበትን ምክንያት ለናስሩዲን ያዋየውና አህያውን በእንክብካቤ እንዲይዘው አደራ ካለው በኋላ ፣ በየዕለቱ መብላት የለመደውን የመኖ መጠን ይነግረዋል ።

«ያንተም በዛ ! አጕል ልማድ ነው ያስተማርከው ፤ ባነሰ መኖ መኖር መቻል አለበት !» አለ ናስሩዲን ።

«እንዲያው አደራህን በየዕለቱ የለመደውን አትንሣው !»

«ግድ የለህም ፤ በራሴ ዘዴ አስተዳድረዋለሁ» ይልና ናስሩዲን አህያውን ይዞ ወደ ቤቱ ይሔዳል ።

ናስሩዲን ለአህያው የሚሰጠውን የመኖ መጠን በየዕለቱ እየቀነሰ ይሔድ ጀመር ። አህያውም ሰውነቱ እየከሳ ይሒድ እንጂ በሚሰጠው አነስተኛ መኖ መኖር የተለማመደ መሰለ ። ይህም ሁኔታ የናስሩዲንን እምነት እያጠናከረው በመምጣቱ ፣ ለአህያው የሚያቀርብለት መኖ 'እንዳይሞት እንዳይሽር' ከሚባልበት ደረጃ ከደረሰ በኋላ ብዙ ቀናት አለፉ ።

በመጨረሻም ፣ አህያው ከታሰረበት ጋጥ ውስጥ ሳይታሰብ ፍግም ብሎ ተገኘ ።

«ያሳዝናል !» አለ ናስሩዲን ፣ አህያው አጠገብ ቆሞ ፤ «በጣም ያሳዝናል ፤ ጥቂት ጊዜ ሰጥተኸኝ ቢሆን ኖሮ ፣ ያለ ምንም መኖ መኖርን አለማምድህ ነበር !»

— አህያ ሠባ ፤ ምን ረባ ።

# በ ጠ ረ ጠ ሩ

ናስሩዲን በአንድ ጭር ባለ አካባቢ ብቻውን ሲንሸራሸር ፣ በርከት ያሉ ሰዎች በፈረስ ላይ ሆነው ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲመጡ ያያል ። ሁኔታውን ለጥቂት ደቂቃ ቆሞ ካስተዋለ በኋላ ፣ የፈረሰኞቹ አመጣጥ በእርሱ ላይ አደጋ የሚያስከትል መስሎ ስለ ተሰማው ፣ እግሬ አውጪኝ ብሎ በመሮጥና በአቅራቢያው የሚገኘውን የግንብ አጥር ዘሎ በማለፍ ፣ ከአንድ ባዶ የመቃብር ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ በጀርባው ተንጋሎ ይተኛል ።

ፈረሰኞቹ የናስሩዲን ሁኔታ ስላስገረማቸው ፣ ከፈረሶቻቸው ላይ ወርደው የሔደበትን አቅጣጫ በመከተል ወደ መቃብሩ ስፍራ ያመራሉ ። እንደ ደረሱም ፣ ናስሩዲን መቃብሩ ውስጥ በጀርባው ተዘርሮ በሐፍርት ሲንዘፈዘፍ ያገኙታል ።

«ከፉኛ ሮጠህ እዚህ የመቃብር ስፍራ ስትገባ አይተን ነው የመጣነው ። ለመሆኑ ምን ነክቶህ ነው እንደዚያ ሮጠህ መጥተህ ጉድጓድ ውስጥ የገባኸው ?» በማለት ይጠይቀዋል—ከፈረሰኞቹ አንዱ ።

ናስሩዲንም ፣ «ጥያቄ በመደርደር ብቻ ልባችሁ የተመኘውን ፣ ሐሳባችሁ የተለመውን እናገኛለን የምትሉ ከሆነ ተሳስታችኋል ። የአንድን ነገር ውል አፈፍ ብሎ ተነሥቶ ለመጨበጥ መሞከር ሞኝነት ነው ። እንዲያው ለነገሩ ብቻ ፣ እኔ እዚህ ጉድጓድ ውስጥ የገባሁት በእናንተ ምክንያት ሲሆን ፣ እናንተም እኔ እገባሁበት ጉድጓድ ድረስ የመጣችሁት በእኔ ሳቢያ ነው» አላቸው ።

— በጠረጠሩ ጠጠር ይጥሉ ።

# ፎክሮ መሸሸ

ናስሩዲንና የቅርብ ጓደኞቹ ቡና ቤት ገብተው ሻይ እየጠጡ ሲጨዋወቱ ፣ «ከእናንተ ውስጥ እኔን የሚወዳደር ለጋስ የለም» በማለት ራሱን ማወዳደስ ጀመረ ።

ከጓደኞቹ አንዱ ቀበል ያደርግና ፣ «ከሁላችንም የበለጥክ ለጋስ ከሆንክ ፣ እስቲ ዛሬ ማታ ቤትህ ወስ ደህ ራት ጋብዘን» አለው ።

ናስሩዲን በግብዣው በመስማማት ጓደኞቹን ሰብስቦ ወደ ቤቱ ይዟቸው ሔደ ። ቤቱ አቅራቢያ እንደ ደረሰ ፣ «እስቲ ላንድ አፍታ እዚህ ቆዩኝ ። እኔ ቀደም ብዬ ልሒድና እንግዶች ይገኙ መምጣቴን ለሚ ስቴ ነግሬአት እመለሳለሁ» አላቸው ።

ሚስቱ የጓደኞቹን ተግበስብሰው መምጣት እን ደሰማች ፣ «እንኳን ይህ ሁሉ ሰው እኔና አንተ የምን ቀምሰው ምግብ ቤት ውስጥ የለም ። በል ፣ እንዲመ ጣሃቸው ቀስ ብለህ መልሳቸው !» አለችው ።

«ይኸማ እንዴት አድርጎ ይሆናል ። ከውጪ ከመለስኳቸውማ በልግስና የታወቀው ስሜ ይጎድ ፋል ፤ ክብሬ ይዋረዳል ።»

«መልካም ፤ እንግዲያው አንተ ፎቅ ላይ ውጣና መኝታ ቤት ገብተህ ተቀመጥ ፤ እኔ እቤት የሌለህ መሆኑን እነግራቸዋለሁ ።»

ከአንድ ሰዓት በኋላ እንግዶቹ ውጪ ቆመው በመጠበቅ ትእግሥታቸው ስለተሟጠጠ የቤቱን በር ከብበው የናስሩዲንን ስም እየጠሩ መጯጯህ ጀመሩ ።

የናስሩዲን ሚስት ወጣ ብላ ፥ «ናስሩዲን እቤት የለም !» አለቻቸው ።

«እንዴት አድርጎ ሊሆን ይችላል ? ከአንድ ሰዓት በፊት አብረነው መጥተን እቤት ሲገባ አይተ ነዋል ። መች ወጣና ነው የለም የምትይን ?» አሏት ፥ በአንድ ድምፅ ።

የናስሩዲን ሚስት የምትመልሰው ነገር ስለ ጠፋት ዝም አለች ።

ሁኔታውን ከፎቅ ሆኖ ይከታተል የነበረው ናስሩዲን ፥ አንገቱን በመስኮት ብቅ አድርጎ ፥ «እባ ካችሁ ሴትዮዋን ግራ አታጋብዋት ! እኔ ብፈልግ በስርቆሽ በር ወጥቼ መሔድ አልችልም ነበር ?» አላቸው ።

— ፎክር መሸሸ ፥ ታሪክ ያበላሽ ።

# ብድር በምድር

ናስሩዲን አልፎ አልፎ ባቅራቢያው የሚገኘውን ሐይቅ በጀልባው ሰዎችን እያሻገረ ገቢ ያገኝ ነበር ። አንድ ቀን አንድ መምህር የናስሩዲንን ጀልባ ተከራ ይቶ ጕዞ እንደ ጀመሩ ፦

«ዛሬ ማዕበል ይነሣ ይሆን?» ሲል ናስሩዲንን ጠየቀው ።

«እኔ አላውቅም ምንም!» በማለት ናስሩዲን መለሰ።

መምህሩም ግራ በመጋባት ፣ «ለመሆኑ ሰዋ ስው የሚባል ነገር ተምረህ ታውቃለህ ?» ሲል ጠየቀው ።

«ስሙንም ዛሬ ገና መስማቴ ነው ።»

«እንግዲያው ኖርኩ አትበል !»

ናስሩዲን ለመምህሩ ምንም መልስ ሳይሰጥ ጕዞ አቸውን ቀጠሉ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐይቁን ነፋስ ያዋክበው ጀመር ። ውኃውም ግራና ቀኝ እየተከለበሰ ጀልባዋ ውስጥ መግባት ያዘ ።

ናስሩዲን ወደ መምህሩ ጠጋ ብሎ ፣ «ለመሆኑ ውኃ ዋና የሚባል ነገር ተምረህ ታውቃለህ ?» አለው ።

«ኧረ የለም ፣ ተምሬም አላውቅ !»

«እንግዲያው ኑሮህ አከተመለት ! ጀልባዋ መስ ጠምዋ ነው» አለው ።

— ብድር አይቀር በምድር ።



# ነገር እንዳገቡት

ናስሩዲን የእህል ፍርፋሪ በማህን ሞልቶ ከዚያ እየቈነጠረ በቤቱ ዙሪያ ሲበትን አንድ መንገድ አላፊ ሰው ያየዋል ።

«ምን እየሠራህ ነው ፥ ናስሩዲን ?»

«ነብሮች ካካባቢው እንዲርቁ እያደረግሁ ነው ።»

«እዚህ አካባቢ ምንም ነብር የለምኮ !»

«እግዜር ይስጥህ ! የምሠራውን ነገር ፍቱንነት ተረድተኸዋል ማለት ነው ።»

— ነገር እንዳገቡት ፥ ሙከት እንዳሰቡት ።

# ነግ፣ በኔ

አንድ ቀን ናስሩዲን እቤቱ የሚገኙትን ድስቶቹን በሙሉ ድግስ ለደረሰበት ጐረቤቱ አዋሰው ። ጐረቤትየውም ድግሱን ካወጣ ቢኋላ የተዋሳቸውን ድስቶች ከአንዲት ተጨማሪ ግልገል ድስት ጋር አምጥቶ ለናስሩዲን አስረከበው ።

«ይህች ትንሿ ድስት ደግሞ ምንድን ናት ?» በማለት ናስሩዲን ጠየቀ ።

«አንተ ያዋስከኝ ድስቶች እኔ ዘንድ በሰነበቱበት ሰሞን የተወለደች ናት ። ባገራችን ወግና ባህል መሠረት ያንተ ንብረት ስለሆነች ከወላጆቿ ጋር አብሬያት ይዤ መጣሁ» አለ ጐረቤትየው—እየሣቀ ።

ጥቂት ሰንብቶ ናስሩዲን ጐረቤቱ ዘንድ ሔዶ ድግስ ያለበት መሆኑን በመግለጽ ፣ እቤት ያሉትን ድስቶች በሙሉ ተዋሰ ። ድግሱም ሳይደግስ የተዋሰውም ዕቃ ሳይመለስ ብዙ ጊዜ አለፈ ።

አንድ ቀን ጐረቤትየው ናስሩዲን ቤት ድረስ በመሔድ ድስቶቹ እንዲመለሱለት ጠየቀ ።

«በጣም አዝናለሁ !» አለ ናስሩዲን ፤ «እጅግ በጣም አድርጌ አዝናለሁ ! ድስቶችህ በሙሉ ስለሞቱብኝ ነው ያልመለስኳቸው ። ባገራችን ወግና ባህል መሠረት ድስቶች መውለድ ከቻሉ መሞት መቻላቸውንም ሳትገነዘበው አትቀርም » አለው ።

# እውነቱን ተናግሮ

«የተለያዩ ሕጎችን በማወጅ ሰዎችን የመልካም ሥነ—ምግባርና የእውነት ተገዥዎች ማድረግ አይቻልም ። ሰዎችን እውነተኞች የሚያደርጋቸው ከዕለት ተዕለት የሕይወት ውጣ ውረድ የሚቀስሙት ግንዛቤ ነው» አለ ናስሩዲን ፣ ከአንድ ንጉሥ ፊት ቀርበ የሐሳብ ልውውጥ በሚያደርግበት ወቅት ።

ንጉሡ የናስሩዲንን ሐሳብ በጥሞና ካዳመጠ በኋላ ፣ ሰዎች እውነትን እንዲናገሩ ፣ እውነተኛውን ነገር እንዲሠሩ ማድረግ የሚቻል መሆኑን በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደሚያሳየው ነግሮት አሰናበተው ።

ሰዎች ወደ ንጉሡ ርዕሰ—ከተማ መግባት የሚችሉት አንድ ትልቅ ወንዝ ላይ የተሠራ ድልድይ ተሻግረው ነበር ። አንድ ቀን ማለዳ ፣ ከድልድዩ አቅራቢያ ሰው መስቀያ እንጨት ተተክሎ ፣ የንጉሡ ዘበኞች ግራ ቀኙን ከብበው ቆመው ይጠብቁ ነበር ። ድልድዩን የሚሻገሩ ሰዎች በአንድ ስፍራ ተሰብስበው እንደ ቆሙ የሚከተለው ትእዛዝ ተሰማ ።

«ይህን ድልድይ የሚሻገር ማንኛውም ሰው አንድ ጥያቄ ይቀርብለታል ። እውነቱን የተናገረ ድልድዩን ይሻገራል ። እውነቱን ያልተናገረ ደግሞ ይሰቀላል !»

ናስሩዲን ከተሰበሰቡት ሰዎች ቀድሞ የዘቦቹ አለቃ ፊት ቀረበ ።

«የት ነው የምትሔደው ?» አለ ፣ የዘቦቹ አለቃ ።

«ልሰቀል መሔዴ ነው !» በማለት ናስሩዲን መልስ ሰጠ ።

«ለመሆኑ 'ልሰቀል መሔዴ ነው' የምትለው ማን ያምነኛል ብለህ ነው ?»

«የተናገርኩት እውነት ካልሆነ ስቀሉኝ !»

«ውሸት ነው የተናገርከው ብለን ብንሰቅልህ ፣ 'ልሰቀል መሔዴ ነው' ብለህ የተናገርከውን ቃል እውነት አድርገን ተቀብልነው ማለት ይሆናል» አለ ፣ የዘብ አለቃው ።

«እርግጥ ነው ይሆናል ። ስለዚህ እናንተ እውነት የምትሉት ሁሉ የሚያዋጣ እውነት አለመሆኑን መገንዘብ ይኖርባችኋል» በማለት ናስሩዲን መለሰለት ።

— እውነቱን ተናግር እመሸበት ማደር ።

## ማን በነገረሽ

ናስሩዲን ከሉካንዳ ቤት ጉበት ገዝቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ፣ አንድ የሚያውቀው ሰው ያገኘውና ስለ ጉበት ምግብ አሠራር የሚያብራራ የባልትና ጽሑፍ ይሰጠዋል ። ከዚያም ወደ ቤቱ በማምራት ላይ እንዳለ ፣ አንዲት ጭልፊት ከሰማይ ስትከንፍ ወርዳ ፣ ናስሩዲን በእጁ የያዘውን ጉበት ነጥቃ ትሔዳለች ።

ናስሩዲን ጭልፊቲቱ ወደምትበርበት አቅጣጫ ቀና ብሎ በመመልከት ፣ «አይ ጅሎ ፤ ባንቺ ቤት የጎዳሽኝ መስሎሻል ! ጉበቱን ብትሞጨልፊም ፣ የባልትናው ጽሑፍ ከእጄ አለመውጣቱን ማን በነገረሽ !» አለ ።

# ልፉ ያለው

ና/ ስሩዲን መሬት ላይ አጐንብሶ አንድ ነገር ሲፈል ግ አንድ መንገድ አላፊ ሰው ያየዋል ።

«መምህር ምን ጠፋብዎት ?» ሲል ሰውየው ጠየቃ ቸው ።

«የበር ቊልፍ መክፈቻዬ ጠፍቶብኝ እየፈለግሁ ነው ።» አለ ናስሩዲን ።

ሰውዬውም ለመምህር ናስሩዲን ያለውን አክ ብ ሮት ለመግለጽ ያፋልገው ጀመር ። ጥቂት ደቂቃ ዎ ችን አካባቢውን አብረው ካሰሱ በኋላ ፥ ሰውዬው ፦

«ለመሆኑ የወደቀበት ቦታ ትዝ አይሎትም ?» አ/ለ ።

«ይለኛል እንጂ !»

«ታዲያ የቊልፍዎ መክፈቻ የትኛው ስፍራ ላይ ነው ጠብ ያለው ?»

«መክፈቻውማ የጠፋው ቤቴ ውስጥ ነው ።»

«መክፈቻው ቤትዎ ውስጥ ከጠፋ እዚህ በመ ፈለግ ለምን ይለፋሉ ?»

«እቤቴ ውስጥ ባለው የጨፍ መብራት ከመ ጨናበስ ፥ በዚህ ጤፍ ሊያስለቅም በሚችለው መብራት መፈለጉ ይሻለኛል ብዬ ነዋ !»

— ልፉ ያለው አንድ እንጨት ያስራል ።



## ውርርድ

ናስሩዲን ፣ በበረዶ በተሸፈነ አንድ ትልቅ ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ አንድ ሌሊት ማደር እንደሚችል በመግለጽ ከጓደኞቹ ጋር ውርርድ ይገጥማል ። ከጓደኞቹ መካከል አንዱ ፣ በዚያ ብርዳማ ተራራ ላይ አንድ ሌሊት ማደር አለመቻሉን በማስረዳት የመወራረጃውን ገንዘብ ይወስናል ። ከመካከላቸው ዳኛ ተመርጦ ሁለቱም ተወራራጆች ገንዘብ ያሲዛሉ ።

ናስሩዲን አንዲት ሻማና አንድ መጽሐፍ ይዞ ተራራው ጫፍ ላይ ይወጣል ። ሌሊቱን ሙሉ ብርድ ሲያቆራምደው አያድሩት አዳር አድሮ በማግሥቱ ጠዋት ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ከተራራው ላይ ይወርዳል ። የውርርዱም ገንዘብ እንዲሰጠው ዳኛውን ይጠይቀዋል ።

«ተራራው ጫፍ ላይ ስትወጣ ሰውነትህን የሚያሞቅ ምንም ነገር አልያዝክም ነበር ?» በማለት ዳኛው ጠየቀው ።

«ምንም አልያዝኩ» አለ ናስሩዲን ።

«አንዲት ሻማ እንኳን አልያዝክም ነበር ?»

«አንዲት ሻማ ይዤ ነበር ።»

«እንግዲያው ተረትተሃል !» አለ ዳኛው ።

ናስሩዲን የዳኛውን ውሳኔ ለመቃወም አልቻ ጣም ። ብይኑን ተቀብሎ ፣ ገንዘቡን አስረክቦ ቤቱ ገባ።

ጥቂት ወራቶች ካለፉ በኋላ ፣ ናስሩዲን በውርርዱ ላይ የነበሩትን ጓደኞቹን በሙሉ ቤቱ ግብዣ ጠራቸው ። በግብዣው ዕለት ሁሉም ተሰብስበው ወደ ቤቱ መጡ ። እንግዶቹ ቤት ውስጥ ተቀምጠው ሲሥቁና ሲጫወቱ የተጠሩበት ግብዣ ሳይቀርብላቸው ብዙ ሰዓት አለፈ ። አንዳንዶቹም አፍ አውጥተው ምግብና መጠጡ ለምን እንደማይቀርብላቸው መጠየቅ ጀመሩ ።

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ፣ «እስቲ ሁላችንም ማድ ቤት ሔደን ምግቡ ደርሶ እንደሆነ እንይ» አላቸው ።

ሁሉም ተንጋግተው ማድቤት ገቡ ። ማድቤቱ ውስጥ አንድ ትልቅ ሰታቴ ድስት ተጥዶ ከሥሩ አንዲት ሻማ ጭል ጭል ስትል ተመለከቱ ። የተጣደው ውኃ ፈልቶ ምግቡን ሊያበስለው ቀርቶ ውኃው ራሱ ገና ለብ አላለም ነበር ።

ናስሩዲን ወደ ጓደኞቹ ዞር ብሎ ፣ «ይኸው እንዳያችሁት ምግቡ ገና አልበሰለም ። ትናንት ይህን ጊዜ ነበር የተጣደው ፤ ምን እንደነካው እንጃ» አላቸው ።

— ውርርድ ፣ ቁም ነገር ይጋርድ ።

# ካነጋገር ይፈረዳል

ዝናብ ከፉኛ ይጥላል ። አጋ አኪል የተባሉ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የተከበሩ የሃይማኖት መሪ ከሚወርደው ዶፍ ለማምለጥ ወደ መጠለያ ሲሮጡ ናስሩዲን ያገኛቸዋል ። «እርስዎን የመሰለ የተከበረ የሃይማኖት አባትና መሪ ከዚህ ከሰማይ ከሚወርደው በረከት ለማምለጥ እንዴት ይሸሻል ? ዝናብ እኮ ለፍጥረት ሁሉ ሕይወት የሚሰጥ የእግዜር ጸጋ እንጂ እንዲህ የሚያስሮጥ ወራሪ ጠላት አይደለም !» አለ ናስሩዲን ፥ መምህሩን መገሰፅ እየቃጣው ።

መምህሩም ናስሩዲን የተናገረው ቃል እውነት መሆኑን በመቀበል ፥ «እውነትም ተሳስቻለሁ ፤ መሮጥ አልነበረብኝም» በማለት በዶፉ ውስጥ ዝግ ብለው ወደ ቤታቸው መንገዳቸውን ቀጠሉ ። አጋ አኪል በዶፉ ርሰው ቤታቸው ከገቡ በኋላ ፥ የብርድ ሕመም ለጥቂት ቀናት ቤት አዋላቸው ።

አንድ ሌላ ጊዜ አጋ አኪል የዝናብ መከላከያ ልብስ ለብሰው በዝናብ ውስጥ ቀስ እያሉ ሲሔዱ ፥ ናስሩዲን ከሚወርደው ዶፍ ለማምለጥ ወደ መጠለያ ሲሮጥ ያገኙትና ፥ «ምነው ናስሩዲን ? አንተ ሌላውን ሰው እየመከርክ ከሰማይ በረከት ራስህ ትሸሻለህ ?» አሉት ።

«ኢኔ እኮ የምሮጠው ፥ እርስዎ የረገጡትን ከሰማይ የወረደ በረከት ፥ በእግሬ እያንቦጫረቅሁ እንዳላረክሰው ብዬ ነው» በማለት ናስሩዲን መለሰ ።

— ካነጋገር ይፈረዳል ፥ ካያያዝ ይቀደዳል ።

## የሚያውቅ ያሳውቅ

የናስሩዲንን ዝና የሰሙ የአንድ መንደር ነዋሪዎች በአንድ በተወሰነ ቀን ሰፈራቸው መጥቶ ንግግር እንዲያደርግላቸው መልእክተኛ ልከው ይጋብዙታል ። ናስሩዲንም ግብዣውን ይቀበላል ።

በቀነ ቀጠሮው የመንደሩ ሰዎች በሙሉ የስብሰባ አዳራሻቸውን ሞልተው ንግግር የሚያደርግላቸውን እንግዳ መምጣት ሲጠባበቁ ፣ ናስሩዲን ልክ በሰዓቱ ከተፍ ይላል ። እንግዳውን የማስተዋወቁ ሥነሥርዓት እንደ ተፈጸመ ፣ ናስሩዲን የመናገሪያው መድረክ ላይ ይወጣና ፣ የተሰበሰበውን ሕዝብ ትኩር ብሎ እየተመለከተ ፦

«የተከበራችሁ አድማጮች ፤ በዛሬው ዕለት ንግግር የማደርግላችሁ ስለ ምን ጉዳይ እንደሆነ ታውቃላችሁ ?» ሲል ይጠይቃቸዋል ።

«ኧረ አናውቅም !» የሚል መልስ አብዛኛው ተሰብሳቢ ያሰማል ።

«ታዲያ ካላወቃችሁ ለምን ታለፋኛላችሁ ። እናንተን የመሰለ አላዋቂ እንዴት ማስተማር ይቻላል ?» በማለት በቊጣ ከመድረኩ ወርዶ ወደ ቤቱ ይሔዳል ።

መንደርተኞቹ በነገሩ ግራ በመጋባት ፣ እስቲ አንድ ጊዜ ደግሞ ጠርተን እንየው በማለት መልእክተኛ ልከው በሚቀጥለው ሳምንት መጥቶ ንግግር እንዲያደርግላቸው ይጋብዙታል ። ናስሩዲን ግብዣውን ይቀበልና በተባለው ቀን ከስብሰባው አዳራሽ በጊዜው ይደርሳል ። አሁን ደግሞ ምን ይናገር ይሆን እያለ አዳራሹን ሞልቶና አሰፍስፎ የሚጠብቀውን መንደርተኛ ትኩር ብሎ እየተመለከተ ፦

«የተከበራችሁ አድማጮች ፤ በዛሬው ዕለት ንግግር የማደርግላችሁ ስለ ምን ጉዳይ እንደሆነ ታው ቃላችሁ ?» በማለት ያለፈውን ሳምንት ጥያቄ ቃል በቃል ይደግምላቸዋል ።

በስብሰባው የተገኙት የመንደሩ ነዋሪዎች ፣ በአንድ ድምፅ ፣ «አዎን ፣ እናውቃለን !» ሲሉ ይመ ልሱለታል ።

«መልካም ፤ እኔ ልንገራችሁ ያሰብኩትን ጉዳይ ካወቃችሁ ፣ ንግግሬን በማሰማት አላደክማችሁም ። ስለዚህ ወደ መጣችሁበት መሔድ ትችላላችሁ» ብሎ አቸው ወደ ቤቱ ይመለሳል ።

የናስሩዲን ሁኔታ የመንደሩን ነዋሪዎች በጣም ግራ አጋባቸው ። በጉዳዩ ከተመካከሩ በኋላ ፣ እስቲ እናስጨርሰው በማለት ፣ በሚቀጥለው ሳምንት ለሦስተኛ ጊዜ መጥቶ ንግግር እንዲያደርግላቸው መልእክተኛ ይልኩበታል ። ናስሩዲንም ጥሪውን ይቀበላል ።

ናስሩዲን በቀጠሮው ቀን ከተፍ ይላል ። መንደ ርተኛውም በነቂስ ወጥቶ ፣ አዳራሹን ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ይጠብቀዋል ። ናስሩዲን መድረክ ላይ ይወጣና ምንም ሐተታ ሳያበዛ ፦—

«ታውቃላችሁ አታውቁም ?» ይላል ፣ በተሰ በሰበው ሕዝብ ላይ እያፈጠጠ ።

«ግማሾቻችን እናውቃለን ፤ ግማሾቻችን ደግሞ አናውቅም !» የሚል መልስ ያገኛል ።

«በጣም ጥሩ ፤ እጅግ በጣም ጥሩ ! እንዲህ ከሆነ ፣ የምታውቁ የማያውቁትን አስተምሩ ፤ የማታውቁ ደግሞ ከሚያውቁት ተማሩ !» በማለት ከመድረኩ ወርዶ ወደ ቤቱ መሰስ አለ ።

# ያልተቀጣ ልጅ

ናስሩዲን አንዲት ጥጃ ጋጥ ውስጥ ለማስገባት ቢወጣ ቢወርድ ከቆመችበት መንቀሳቀስ አሻፈረኝ አለች ። ናስሩዲንም ፣ ጥጃዋን ይተውና ወደ እናትዋ በመዞር ዘለፋና ስድብ ያወርድባት ጀመር ።

አንድ በዚያው በኩል የሚያልፍ ሰው ፣ «ላም ዋን ምን አድርጊ ብለህ ነው እንደዚህ የምትወርድ ባት ?» ሲል ናስሩዲንን ይጠይቀዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «ታዲያ ምን አድርግ ትለኛለህ ! ይህችን ሞገደኛ ልጅዋን መከራና ዘክራ አላሳድግ ስትል !» አለው ።

— ያልተቀጣ ልጅ ፣ ያልታጠበ እጅ ።

# ልጅን መርገም

አንዲት ሴትዮ ናስሩዲን ዘንድ ልጅዋን ይዛ ትመጣና እንዲህ ብላ ትለምነዋለች ፤—

«ይኸ ልጄ ዐመሉ ከዕለት ዕለት እየከፋ ሔዷል። ቢመቱት ፥ ቢመክሩት ጨርሶ የማይሰማ ሆኖብኛል ። መቼም እርስዎ አስተማሪው ስለሆኑ እስቲ ይሻለው እንደሆን በቊጣም በተግሣፅም እንዲያስፈራሩልኝ ነው ይዤው የመጣሁት ።»

ናስሩዲን የልጁን እናት ችግር በጥሞና ካዳመጠ በኋላ ፥ ወደ ልጁ ዞር ብሎ ፥ ዓይኑን ብልጥጥ ድርግም ፤ ፊቱን ቅጭም ፤ ጥርሱን ግጥም ፤ ዓይኑን እንደገና ፍጥጥ ፤ አፉን ክፍት እያደረገ ምድር አልበቃው ብሎት ከቦታ ቦታ መዝለል ፥ መወራጨትና መንቆራጠጥ ያዘ ። በመጨረሻም ከቤት ውስጥ ዘሎ ሲወጣ የልጁ እናት ከድንጋጤዋ ብዛት የተነሣ ሕሊናዋን ሳተች ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ናስሩዲን ከውጪ ፊቱን ቅጭም አድርጎ ወደ ቤት እያዘገመ ገባ ።

ሴትዮዋ ነፍስ ከዘራች በኋላ ፥ «ምነው መምህር ፤ ምን ብበድልዎት ነው ልጄን ያስፈራሩልኝ ብልዎት እኔን እንዲህ አድርገው ሕይወቴን እስክስት ያስደነገጡኝ ?» አለች ።

«የኔ እመቤት ፤ የደነገጡት እርስዎ ብቻ አልነበሩም ። እኔ እንደዚያ ከቤት ተፈናጥሬ የወጣሁት የራሴ ሁኔታ ስላስደነገጠኝ ነበር !» አለ ።

— ልጅን መርገምና ራስን መጸዳዳት ተመልሶ ጕዳት ።



# የሰው ወርቅ አያደምቅ

ጃላል የተባለ የብዙ ዘመን ጓደኛው ናስሩዲንን ሩቅ አገር አቋርጦ ሊጠይቀው ይመጣል ። ናስሩዲን ወደ አንድ ስፍራ ለመሔድ ዝግጅት ሲያደርግ ሁለቱ ጓደኞሞች ይገናኛሉ ። የናፍቆት ሰላምታ ከተለዋ ወጡ በኋላ ፣ «ልትጠይቀኝ በመምጣትህ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ሳንተያይ ብዙ ጊዜ ሆነን ። እኔ አሁን አንድ ሦስት ቦታዎች ደርሼ ለመመለስ አስቤአለሁ ። አብረን እየተጨዋወትን እንሒድ» አለው — ናስሩ ዲን ።

«አብረን እንሒድ ካልክ ልብስ አውሰኝና እን ሔዳለን ። እንደምታየኝ የለበስኩት ልብስ ስላደፈ በዚህ ሁኔታ ሰው ፊት ብቀርብ አንተንም አስገምት ሃለሁ» አለ — ጃለል ።

ናስሩዲን ከልብሶቹ ደህናውን መርጦ ለጓደኛው ሰጠው ። ጃላል ሰውነቱን ተጣጥቦ ፣ ፊቱን አወዛዝቶ ልብሱን ከለወጠ በኋላ ፣ ሁለቱ ጓደኞሞች እየተጨ ዋወቱ መንገድ ጀመሩ ።

መጀመሪያ ሊጎበኙት ካሰበው ቤት ጉራ እን ዳሉ ፣ የቤቱን ሰዎች ፣ «የብዙ ዘመን ጓደኛዬን ጃላ ልን ተዋወቁልኝ ። ጃላል የልብ ወዳጄ ነው ፤ የለበ ሰው ልብስ ግን የእኔ ነው» አላቸው—ናስሩዲን ።

የመጀመሪያውን ቤት ጉብኝት ፈጽመው ወደ ሁለተኛው ስፈር በማምራት ላይ ሳሉ ፣ ጃላል ፣ ልቡን ይከነክነው የነበረውን ቅሬታ እንዲህ ሲል ለጓደኛው ይገልጽለታል ፤ «ወዳጄ ናስሩዲን ፤ ቅድም የተናገር ከው ነገር በጣም ቅር አሰኝቶኛል ። እንዴት 'የለበ ሰው ልብስ የእኔ ነው' ብለህ በማላውቃቸው ሰዎች ፊት ታሳፍረኛለህ ?»

ናስሩዲን ጓደኛውን ይቅርታ በመጠየቅ ሁለ ተኛ እንደማይለምደው ቃል ገብቶለት መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ሁለተኛው ቤት እንደ ደረሱ ባለቤቶቹ በደ ስታ ተቀብለው ሲያስተናግዷቸው ፣ ናስሩዲን ፣ «ያ፡ኸ ውላችሁ ይህ ዛሬ አብሮኝ ያለው ጓደኛዬ ፣ ጀላል ይባ ላል ። ጀላል ፣ አፈር ፈጭተን ውኃ ተራጭተን አብ ሮኝ ያደገ ጓደኛዬ ነው ። የለበሰው ልብስ ግን የራሱ ነው» በማለት አስተዋወቀው ።

የመጨረሻውን ስፍራ ለመጐብኘት መንገድ እንደ ጀመሩ፣ ጀላል ማኩረፉን ናስሩዲን በመረዳት ፤—

«ምነው ዝም አልክ?» ብሎ ይጠይቀዋል ።

«ታዲያ ምን ልበል፤በየደረስንበት ስታሳፍረኝ!»

«መጀመሪያ ልብሱ የእኔ ነው አልኩ ፤ አሁን ደግሞ ሳፊ ለሳፊ እንሁን በማለት ልብሱ የርሱ ነው አልኩ ። ታዲያ ምን አጠፋሁ ነው የምትለኝ ?»

«ስማ ናስሩዲን ፤ ከአሁን በኋላ ስለ ልብሱ አን ዲት ቃል እንኳን እንዳትተነፍስ ። አለበለዚያ የመ ረረ ጸብ እንጣላለን !»

«እሺ ፣ ከአሁን በኋላ ስለ ልብሱ አንዲት ቃል እንኳን ትንፍሽ አልልም !» አለ ናስሩዲን ፣ የወዳጁን ትከሻ መታ መታ እያደረገ ።

ሦስተኛው ቤት ገባ እንዳሉ ፣ ናስሩዲን ለቤቱ ጌቶች ፣ «ጓደኛዬን ጀላልን ተዋወቁልኝ ። ጀላል የልብ ጓደኛዬ ነው ። እና ፣ የለበሰው ልብስ ... አሁን ለብሶት የምታዩት ልብስ ... እንዲህ አምሮበት የም ታዩት ልብስ ... አይ ፣ እንዲያው ለነገሩ ነው እንጂ ፣ ስለ ልብሱ ብዙም ባላወራ ይሻለኛል» በማለት ጀላ ልን ኩም አደረገው ።

— ከይሉኝ አይል ፣ አይብ አትብላ ።

## ዕዳ ከሜዳ

ውድቅት ላይ ሁለት የሰከሩ ሰዎች ተጣልተው ሲንጫጩ ናስሩዲን ከእንቅልፉ ብንን ብሎ ይነሣል ። አልጋው ላይ ሆኖ ሲያዳምጥ የሰዎቹ ጸብ እየከረረ ፣ ጩኸታቸውና ንትርካቸው እየጨመረ መሔዱን ሲረዳ ፣ በብርድልብሱ ጥቅልል ብሎ በሩን ከፍቶ ይወጣና ሰዎቹ ጸባቸውን አቁመው በሰላም ወደ ቤታቸው እንዲገቡ በመምከር ሊገላግላቸው ሙከራ ያደርጋል ። በዚህ ጊዜ ከሁለቱ ሰካራሞች አንዱ የናስሩዲንን ብርድልብስ መንትፎ ፈትለክ ይላል ። ሁለተኛው ሰውዬ ናስሩዲን ራቁቱን መቅረቱን ሲያይ እርሱም የነፍስ አውጪኝ ይሮጣል ።

ናስሩዲን በሩን ዘጋግቶ ቤቱ እንደገባ ፣ ባለቤቱ ፣ «ምን ነበር እንዲህ ያጣላቸው ?» ብላ ትጠይቃለች ፣ ተከናንባ እንደ ተኛች ።

«በብርድልብሴ ምክንያት መሆን አለበት ። ብርድልብሴን እጃቸው እንዳገቡ ጸባቸውን አቁመው ሁለቱም እግሬ አውጪኝ ብለው ተፈትለኩ !» አላት ።

— ዕዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ ።



# ላንዱ ፍስሐው ለአንዱ ሐዘኑ

ናስሩዲን ሕንድ አገር በጉብኝት ላይ ሳለ ፣ በቅርጹና በታላቅነቱ ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀው ሕንፃ ዘንድ ይደርሳል ። የሕንፃውን ድንቅ አሠራር ለመመልከት ወደ በራፉ እንደ ተጠጋ አንድ መናኝ መግቢያው በር ላይ በጽዋሜ ተጠምዶ ያገኘዋል ። ናስሩዲን ፣ በመናኙ የመንፈስ ተመስጦ ፣ በገጹ ላይ በሚታየው እርጋታና ፀዳል በመሳብ ሊጐበኘው ያሰበውን ሕንፃ ይረሳል ።

በሐሳቡም ፣ «እኔን የመሰለ የወጣለት ተፈላሳፊ ይህን ከመሰለ የበቃና ዓለምን የናቀ መናኝ ጋር አቀራርቦ የሚያወያይ ቁም ነገር መኖር አለበት» በማለት መናኙ ወደ ተቀመጠበት ቀረብ ብሎ ሰላምታ ይሰጠዋል ።

መናኙም ፣ «እኔ ዮጊ ነኝ ። የሕይወት ዓላማዬም ለፍጥረታት ደኅንነት ማሰብና መጨነቅ ነው ። በተለይ ደግሞ ለአዕዋፋትና ለዓሦች ደኅንነት ከሁሉም የላቀ ትኩረት እሰጣለሁ» ይለዋል ።

«እንዲህ ከሆነ አብሬህ እንድሰነብት መልካም ፈቃድህ ይሁን» በማለት ናስሩዲን መናኙን በመለመን ፣ «እኔ ገና ሳይህ ነው ከአንተ ጋር በጥብቅ የሚያስተሳስር የጋራ እምነት እንዳለኝ የተሰማኝ ። በአንድ ወቅት አንድ ዓሣ ሕይወቴን ከሞት በማዳኑ ለዓሦች የሚሰማኝ ባለውለተኛነት በጣም ከፍተኛ ነው» አለው ።

«እንዴት ያለው ግሩም አጋጣሚ ነው !» አለ ዮጊው ፤ «ከእኔ ጋር እንድትሰነብት በደስታ እቀበልሃለሁ ። እስከ ዛሬ ለፍጥረታት ደኅንነት ስጥርና

ስግር ብኖርም ፥ ከእንስሳት ጋር እንደ አንተ ቅርበት ኖሮኝ አያውቅም ። ዓሣ ነፍሴን አዳናት አይደል ያልከኝ ? ይኸውልኽ ፤ በአንተ ላይ የደረሰው መል ካም ነገር ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት በሙሉ ተደ ጋጋፊ ናቸው የሚለውን እምነቴን እጅጉን ያጠናከ ረዋል ።»

ናስሩዲን ከመናኙ ጋር ሕንፃው ደጃፍ ተቀምጦ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመለማመድ ፥ እግሮቹን አጣምሮ ፥ እጆቹን በጉልበቱ ላይ አነባብሮ የሕይወትን ምስጢር በማስተንተን ጥቂት ሳምንታት አሳለፈ ።

አንድ ቀን መናኙ ናስሩዲንን እንዲህ አለው ፤ «እንግዲህ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ይኸው አብረን ሰንብተናል ፤ በበለጠም ለመቀራረብና ሐሳብ ለሐ ሳብ ለመተዋወቅ በቅተናል ። እባክህን ያ የተባረከ ዓሣ ሕይወትህን እንዴት አድርጎ እንዳዳነ አጫው ተኝ !»

«አብረን ባሳለፍናቸው ሳምንታት ውስጥ ያን ተን እምነት በመጠኑም ቢሆን የተረዳሁት ስለሚመ ስለኝ የዓሣውን ታሪክ ላንተ ማጫወቱ የሚበጅ አይ መስለኝም» አለው—ናስሩዲን ።

መናኙም ፥ ከናስሩዲን ፊት እየወደቀና እየተነሣ የዓሣውን ነፍስ—አድን ድንቅ ታሪክ እንዲያወ ጋው በመማጸን ፋታ ነሣው ።

ናስሩዲን ቢጨንቀው ፥ ለመናኙ እንዲህ ሲል ቊርጡን ነገረው ፤ «የዓሣውን ፍጡነ—ረድኤትንት ታሪክ ካልነገርከኝ ብለህ ካስቸገርከኝ እኔ በበኩሌ ታሪኩን ላወጋህ ዝግጁ ነኝ ። ሳስበው ግን የምነግር ህን የዓሣውን ታሪክ ሰምቶ ለመቀበል አስፈላጊው

የሥነ—ልቦና ዝግጅት ያለህ አይመስለኝም ። ቢሆ
ንም ካልነገርከኝ ብለህ ካስቸገርከኝ ፣ ታሪኩ እንዲህ
ነው ። ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩልህ ዓሣው ሕይወቴን
ማዳኑ የማይታበል ሐቅ ነው ። ታዲያ ፣ አንድ ጊዜ
የምልሰው የምቀምሰው በማጣቴ የተነሣ ረሃብ ሲገድ
ለኝ በመሆኑ ፣ ከመሞት መሰንበት በማለት መን
ጠቆ አዘጋጀሁና በአቅራቢያዬ ወደሚገኘው ወንዝ
አመራሁ ። እዚያም ብዙ ሳልቆይ አንድ ትልቅ ዓሣ
ያዝኩ ። ቤቴ ወስጄ ሦስት ቀን ሙሉ እንክት አድ
ርጌ በላሁት !»

— ያንዱ በሬ ሲሞት፣ላንዱ እጋዘኑ፣ላንዱ ፍስሐው፣ላንዱ ሐዘኑ ።

## አፍ ያለው

አንድ ቀን ሌሊት ቤቱ ውስጥ ሌቦች ገብተው
ሲንጐዳጐዱ ናስሩዲን ሰምቶ ፍርሐት ስለ ያዘው
ቁምሣጥኑ ውስጥ ገብቶ ይደበቃል ። ሌቦቹ ቤቱ
ውስጥ የሚረባ ነገር ፈልገው ስላጡ ቁምሣጥኑን
ይከፍታሉ ። ናስሩዲንን ቁምሣጥኑ ውስጥ ጭብጥብጥ
ብሎ ተቀምጦ ያገኙታል ።

«ለምንድን ነው ቁምሣጥኑ ውስጥ የተደበቅ
ኸው ?» በማለት አንዱ ሌባ በቍጣ ናስሩዲንን ይጠ
ይቀዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «እዚህ ቁምሣጥን ውስጥ እንዲህ
ዙርምት ብዬ የተደበቅኩት ፣ እናንተን ደስ የሚያ
ሰኝ ነገር እቤቴ ውስጥ አለመኖሩ አሳፍሮኝ ነው»
አላቸው ።

— አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል ።



# ነገር እንደ አፉ

ናስሩዲን አንድ ውብና ዋጋው ውድ የሆነ የእጅ ቀለበት መንገድ ላይ ወድቆ ያገኛል። ቀለበቱን መሬት ወድቆ ማግኘቱን ለሰው እንዳይናገር በጣም ያጣ ጣዋል ። ያገሩ ሕግ ደግሞ ፣ ዕቃ መሬት ወድቆ ያገኘ ሰው ፣ ገበያ መካከል ቆሞ ፣ ያገኘውን ዕቃ ስም ከፍ ባለ ድምፅ ሦስት ጊዜ እየጠራ እንዲያስታውቅ ያዛል።

ናስሩዲን ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ፣ አቅራቢያው ከሚገኘው ገበያ መካከል ቆሞ ፣ «አንድ የጣት ቀለ በት ወድቆ አግኝቻለሁ !» በማለት ጮኾ ይናገራል ።

ቀለበቱን ወድቆ ማግኘቱን ለሦስተኛ ጊዜ ተና ግሮ እንዳበቃ ፣ በገበያው አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ከያቅጣጫው ብቅ ብቅ በማለት ናስሩዲን ከቆመበት ስፍራ ይደርሳሉ ።

«የምን አዋጅ ነበር በውድቅት ታሰማ የነበ ረው ?» በማለት ሰዎቹ ናስሩዲንን መጠየቅ ይጀምራሉ ።

«አይ! ሕጉ እንኳን ይህንን ጉዳይ ሦስት ጊዜ ብቻ ተደጋግሞ እንዲነገር ነው የሚያዘው ። ለእናንተ ብቻ አራተኛ ጊዜ ብደግመው ሕጉን መተላለፍ ይሆን ብኛል ። ቢሆንም ፣ አንድ ሌላ ነገር እንድታውቁልኝ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ ። ከአሁኗ ቅጽበት ጀምሮ አንድ ከአልማዝ የተሠራ የጣት ቀለበት ባለቤት ሆኛለሁ» አላቸው ።

— ነገር እንዳፉ ፣ ዛፍ እንደ ቅርንጫፉ ።

# አፍ ነገር ዓይን አገር

አንድ ማይም ናስሩዲን ቤት ድረስ ይሔድና ሩቅ አገር ለሚኖር ዘመዱ ደብዳቤ እንዲጽፍለት ይለ ምንዋል ።

«እግሬን ስላመመኝ ልጽፍልህ አልችልም !» ይላል—ናስሩዲን ።

«የእግርህ መታመም ለእኔ አንዲት ብጣሽ ወረ ቀት ከመጻፍ ጋር ምን አገናኘው ?» በማለት ሰው ዬው ይጠይቃል ።

ናስሩዲንም ፥ «ለዘመድህ የምጽፍልህን ደብዳቤ እኔው ራሴ ይዤ ሔጄ ካላነበብኩለት ፥ የእኔን ሙን ጭርጭር ጽሕፈት እስከዛሬ ድረስ ሊያነብ የሚችል ሰው ባለመገኘቱ ደብዳቤውን ብጽፍልህም ከንቱ ልፋት በመሆኑ በጊዜ ሌላ ሰው ፈልግ» አለው ።

— አፍ ነገር ዓይን አገር እያጣም ።

# እ ዛ ኝ

ናስሩዲን ለማገዶ የሚሆን እንጨት ከጫካ ቈርጦ ሁለት ሦስቱን ግንድ በአህያው እያስጐተተ ወደ ቤቱ ሲያመላልስ ይቆይና ደከም ሲለው ከሚ ጐተቱት ግንዶች ላይ ተፈናጦ ሲሔድ ያየው ሰው ፡—

«መቀመጥህ ካልቀረ ግንዱ ላይ ከምትፈናጠጥ ለምን አህያው ላይ ተደላድለህ ተቀምጠህ አትሄ ድም ?» ይለዋል ።

«ምነው ምን አደረግሁህ ፣ ወዳጄ ! አህያው ይህን ሁሉ ግንድ እየጐተተ መሔዱ አንሶት እላዩ ላይ ተቀመጥበት ትለኛለህ ? እንዲያው ምን ዓይነቱ ጨካኝ ብትሆን ነው እንዲህ ያለ ምክር የምትለግሰኝ ? እኔ እንደሆንኩ ከዚህ ግንድ ላይ ንቅንቅ አልልም» በማለት ናስሩዲን መለሰለት ።

— አዛኝ ቅቤ አንጓች ።

## አንድ እግረኛ ያወራው

«አንድ ጊዜ ብቻዬን በረሃ አቋርጬ ስጓዝ ፣ አንድ ስፍራ ሰብሰብ ብለው የተቀመጡ ሽፍቶች አገኘሁ ፣ ልባቸው እስኪፈርስ እንዲሮጡ አደረግኋቸው !» አለ ናስሩዲን—እየተኩራራ ።

«እንዴት አድርገህ በል ?» በማለት ጓደኛው ጠየቀው ።

«ምንም ችግር አልነበረበትም ። እኔ ገና እንዳየኋቸው ይገድሉኛል ብዬ ፈርቼ እግሬ አውጪኝ አልኩ ። እነሱም ተከተሉኝ !» አለ ናስሩዲን ።

— አንድ እግረኛ ያወራውን አንድ ፈረሰኛ አይመልሰውም ።



# ጥጃ ቢፈነጭ

የፈረስ ግልቢያ እሽቅድምድም በሚደረግበት ሰጥ ያለ ሜዳ ላይ አያሌ ፈረስ ጋላቢዎች ተሰብስበው ውድድሩ የሚጀመርበትን ጊዜ ሲጠባበቁ ፣ ናስሩዲን አንድ በሬ ላይ ተቀምጦ ወደ ውድድሩ ቦታ ሲገባ ሰዎች ያዩታል ።

«ኩመቹ ወዲህ ነው ደግሞ በሬ ለግልቢያ የሚያገለግለው ?» በማለት ከሰዎቹ መካከል አንዱ ናስሩዲንን ይጠይቀዋል ።

«በሬ አይጋልብም ያለህ ማነው !» አለ ናስሩዲን ቈጣ ብሎ ። «እኔ ይህንን በሬ ከልጅነቱ ጀምሮ ነው የማውቀው ። ጥጃ በነበረበት ጊዜ በየመስኩ ላይ ሲቦርቅ ጋላቢ የተባለ ፈረስ አይደርስበትም ነበር ። ታዲያ በእምቦሳነቱ እንደዚያ የሮጠ አሁን እንዲ ካደገ በኋላ ከፈረስ ይበልጥ የማይጋልብበት ምን ምክንያት አለ ?» በማለት መለሰለት ።

— ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ፣ ውኃ ቢሮጥ በጐድጓዳ ።

# ከሆነ ወዲያ

አንድ ቀን ናስሩዲን አንድ ኪሎ የልብስ ሳሙና ገዝቶ ወደ ቤቱ ይወስድና ሚስቱን እጀጠባቤን እጠቢበት ብሎ ይሰጣታል ።

ባለቤቲቱም የማድ ቤት ሥራዋን ጨራርሳ የናስሩዲንን እጀጠባቦች ውጭ አውጥታ ለማጠብ ውኃ ነክራ ሳሙና ለመምታት ስትዘጋጅ ፣ አንድ ጥንዚዛ የመሰለ ቁራ ከተፍ ይልና ሳሙናውን መንትፎ በመብረር ከአንድ ዛፍ ጫፍ ላይ ወጥቶ ቁጢጥ ይላል ። የናስሩዲን ሚስትም በሁኔታው በመደናገጥ እሪታዋን ታቀልጠዋለች ።

ናስሩዲን ደንግጦ ከቤት በመውጣት ፣ ሚስቱ ወደ ሰማይ አንጋጣ ስትጮህ ያገኛትና ፣ «ምነው ምን ነካሽ ? እረ ምነው ምን ሆንሽ ?» ይላታል ።

«እጀጠባቦችህን ለማጠብ ስንደፋደፍ ፣ እየውልህ ፣ ያ ትልቅ ቁራ መጥቶ ሳሙናውን መንትፎት ሔደ !» ትለዋለች ።

ናስሩዲንም እርጋታ በተሞላበት ሁኔታ ቁራውን ቀና ብሎ ከተመለከተ በኋላ ፣ «አይዞሽ አትረበሺ ። እስቲ የኔን እጀጠባብና ቁራው የለበሰውን ልብስ ተመልከቺው ። ሳሙናውን የወሰደው እሱ ከኔ የበለጠ ንጽሕና ስለሚያስፈልገው በመሆኑ ምንም መናደድ የለብሽም» አላት ።

— ከሆነ ወዲያ ንዴት ለሽበት ።

# የ ለ በ ሰ

በአቅራቢያው የሚኖር አንድ መስፍን ፣ ድል ያለ ድግስ የሚያበላ መሆኑን ናስሩዲን ይሰማና ወደ ዚያው ይሔዳል ። ከስፍራው እንደ ደረሰ ፣ የለበሰ ውን ልብስ መናኛነት የተመለከቱ አጋፋሪዎች ተቀ ብለው በአዳራሹ ውስጥ አንድ ስርቻ ፈልገው ይወ ሽቁታል ። ናስሩዲን የተቀመጠበት ቦታ ፍርፋሪ እንኳን የማይደርስበት መሆኑን በመገንዘቡ ፣ ከአዳ ራሹ ሹልክ ይል ይወጣና ወደ ቤቱ ፈጥኖ ይሔዳል ።

ከዚያም የክት ልብሱን ግጥም አድርጎ ይለብ ስና በአስቸኳይ ወደ ድግሱ ስፍራ ይመለሳል ። መስ ፍኑ ግቢ እንደ ደረሰ እንግዳ ተቀባዮቹ የከበሮና የእም ቢልታ ድምፅ ያሰሙለታል ። የአጋፋሪዎቹ አለቃም እበር ድረስ ወጥቶ ይቀበለውና መስፍኑ አቅራቢያ በክብር ስፍራ ላይ ያስቀምጠዋል ። አፍታ ሳይቆይ ምርጥ ምግብና መጠጥ ይቀርብለታል ።

ናስሩዲን ከእንጀራው እየቈረሰ ፣ ከወጡ እያጠ ቀሰ የክት ልብሱን ከዳር እስከ ዳር ይለቀልቅ ጀመር ። ሁኔታውን ከሩቅ ሲመለከት የነበረው መስፍን ፣ ናስሩ ዲን እተቀመጠበት ስፍራ ድረስ መጥቶ ፡—

«ክቡር ሆይ ፤ ያበላልዎ ባህል እስከ ዛሬ አይ ቼው የማላውቀው ስለ ሆነብኝ ግራ ገብቶኝ ነው ቀረብ ብዬ ላነጋግርዎት በማለት እዚህ ድረስ የመ ጣሁት ። የተጋበዙት ራስዎ ሆነው ሳለ ከምግቡ ምንም ሳይቀምሱለት እንሥተው ልብስዎን የሚለ ቀልቁበት ምስጢሩ ምን ይሆን ?» ብሎ ጠየቀ ።



ናስሩዲንም ከተቀመጠበት ተነሥቶ እጅ በመንሣት ፣ «እርግጥ ፣ ድግስዎን መብላት የነበረብኝ እኔው ራሴ ነበርኩ ። ከሁሉ አስቀድሜ ልገልጽልዎት የምሻው በዛሬው ቀን እርስዎ ግቢ ግብር ለመብላት ሁለት ጊዜ መምጣቴን ነው ። መጀመሪያ ስመጣ ፣ አጋፋሪዎችዎ የልብሴን አዳፋነት በማየት አዳራሹ ውስጥ አንድ ስርቻ ፈልገው ይሸጉጡኛል ። እኔም ሁኔታው የማያዋጣ መሆኑን ስረዳ ፣ ከአዳራሹ ወጥቼ ወደ ቤቴ በመሔድ የክት ልብሴን ለብሼ ብመለስ በከበሮና በእንቢልታ አቀባበል ተደረገልኝ ፤ የአጋፋሪዎችዎ አለቃም ከደጅ ተቀብሎ የክብር ቦታ ላይ አስቀመጠኝ ፤ ምርጥ የሆነ ምግብና መጠጥ ቀረበልኝ ። ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ እኔነቴ ሳይሆን ፣ ልብሴ በመሆኑ በቅድሚያ ይድረሰው ብዬ ነው» ሲል መልስ ሰጠ ።

— የለበሰ የማንንም ጒረሰ ።

## ዓይን አይቶ

ናስሩዲንና ጓደኛው ቤት ውስጥ ተቀምጠው ሲጫዋወቱ ቀኑ እየመሸ ለዓይን መያዝ ይጀምራል ።

ጓደኛው ናስሩዲንን ፣ «እየጨለመ እኮ ሔደ ። እስቲ ሻማውን አብራው ። ያውልህ ፣ አንዱ ሻማ በግራህ በኩል አለልህ» ይለዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «ምን ማለትህ ነው ? ከጨለመ ግራና ቀኙን በምን አባቴ መለየት እችላለሁ!» አለው።

— ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል ።

## ሰው ከመከረው

ናስሩዲን ሰውን በቃላት ውርጅብኝ ከማጣደፍ ይልቅ በምሳሌና ተግባራዊነት በሠረፀው ዘዴ ማስተማር ይቻላል የሚል ጽኑ እምነት ነበረው ።

ከዕለታት አንድ ቀን እያፈሰሰ ያስቸገረውን የቤቱን ጣሪያ ሲጠጋግን ፣ በሰፈሩ በድህነቱ የታወቀ አንድ ሰው ይመጣና ፣ «እባክህ ናስሩዲን ዛሬ ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሃለሁ ። አንድ ጊዜ ወረድ በልና ላነጋግርህ» ይለዋል ።

ናስሩዲንም ቶሎ ብሎ ከቤቱ ጣሪያ ላይ ይወርዳል ።

በዚህ ጊዜ ሰውዬው ወደ ናስሩዲን ጠጋ በማለት ፣ «እባክህ በጣም ቸግሮኛል ፤ እስቲ የምትችለውን ያህል ተመጽውተኝ» ይለዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «የመጣኸው ምጽዋት ፍለጋ ከሆነ ጣራው ላይ እንዳለሁ ለምን አልጠየቅኸኝም ?» በማለት ሰውዬውን በቍጣ ይገሥፀዋል ።

«ሰው እንዳይሰማኝ ፈርቼ ነው ።»

«እንዲያው ዝም ብለህ ነው እንጂ ምን የሚያስፈራ ነገር አለበት» ይለውና አብሮት ጣሪያው ላይ እንዲወጣ ይጋብዘዋል ። ሁለቱም ጣሪያው ላይ እንደ ወጡ ፣ ናስሩዲን አቋርጦት የነበረውን ሥራ እየከወነ ፣ «አዝናለሁ ፤ ዛሬ በእጄ ምንም ገንዘብ ስለሌለኝ ልመጽውትህ አልችልም !» ይለዋል ።

— ሰው ከመከረው ፣ መከራ የመከረው ።

# ይበጃል ያሉት

ናስሩዲን ባንድ ወቅት የሚኖርበት አካባቢ የዳኝነት ሥራ ተሰጥቶት ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን ፣ ችሎት ላይ ተሠይሞ እንዳለ ፣ አንድ ሰው ፍርድ ቤቱ ውስጥ እየሮጠ ገብቶ ናስረዲን ፊት በመቆም ፣ «ክቡር ሆይ ፤ ከዚህ መንደር ወጣ ብሎ በሚገኝ አንድ አሳቻ ስፍራ ሌቦች አድፍጠው ይዘው ፣ የለበስኩትን ልብስ ከላይ እስከ ታች ገፈው ፣ የእግር ጫማዬ ሳይቀር አውልቀው ወስደውብኛልና ተፈልገው ተይዘው እፊትዎ ቀርበው ንብረቴ እንዲመለስልኝና ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ ይደረግልኝ !» በማለት ያመለክታል ።

ናስሩዲን ሰውዬውን ከላይ እስከ ታች ደህና አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ፣ «ሌቦቹ ካኔቴራህንና ሙታንታህን አልወሰዱብህም ማለት ነው ?» ሲል ይጠይቀዋል ።

«ካኔቴራና ሙታንታዬንማ ይኸው ለብሼዋለሁ፤ እሱን አልወሰዱብኝም ።»

«እንግዲያው ጉዳይህን ማየት አልችልም ። ሌቦቹ የኛ ክልል ነዋሪዎች አይደሉም ። ቢሆኑ ኖሮ ምንም አያስቀሩልህም ነበር!» አለው ።

— ይበጃል ያሉት ኩል ዓይን አጠፉ ።



# ነገር የሚከረው

የናስሩዲን ሚስት ከባድ የሆነ የመውደቅ ድምፅ ትሰማና እየሮጠች የባልዋን መኝታ ቤት በርግዳ ገብታ ፤ «ምነው ደህና አይደለህም እንዴ ? ምንድን ነው እንዲህ ድው ብሎ የወደቀው ?» ትለዋለች ።

«አይ ፤ ይህን ያህልም የሚያሠጋ ነገር አይደ ለም ። እጀጠባቤ ነው ከተሰቀለበት የወደቀው» በማ ለት ናስሩዲን ይመልስላታል ።

«እንደዚያ ቤቱ እስኪነቃነቅ የወደቀው እጀ ጠባቤ ነው እንዳትለኝ !»

«አይ አልልሽም ፤ እኔም ውስጡ ነበርኩ !» አላት ።

— ነገር የሚከረው ጕንጓኑን ሲያገኝ ነው ።

# ተዋጊ በሬ

የጐረቤት ተዋጊ በሬ የናስሩዲንን አጥር ጥርም ስምሱን አውጥቶ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ ፣ ናስሩዲን ይደርስበትና በያዘው ዱላ ክፉኛ ሲነርተው ባለቤቱ ከቤት ይወጣል ።

«ለመሆኑ እንዴት ብትጠግብ ነው በሬዩን እን ዲህ አድርገህ የምትመታው ?» በማለት ባለቤትዬው እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ ናስሩዲንን ይጠይቀዋል ።

«አንተን ምንም የሚያገባህ ነገር የለም ! የሠ ራውን ሥራ በሬህ ራሱ ደህና አድርጎ ያውቀዋል ። ስለዚህ የሚዋጣልን እኔና እርሱ ስለሆንን አርፈህ ተቀመጥ !» አለ—ናስሩዲን ።

— ተዋጊ በሬ ተጭድ ይ[illegible] ።

# ወፍ እንዳገርዋ

ናስሩዲን ማሳ ውስጥ ገብቶ ፍሬ እየቀጠፈ ሲበላ ባለቤቱን ከሩቅ ሲመጣ ስላየው ዛፍ ላይ ወጥቶ ይደበቃል ።

«ሮጠህ ዛፍ ላይ የወጣኸው ምን ለመሆን ነው?» በማለት የማሳው ባለቤት ናስሩዲንን ይጠይቀዋል ።

«ለመዝፈን ነው ፤ የጨረባ ዘፈን ለመዝፈን ።»

«እሺ ፥ የኛ ጨረባ ! እስቲ ዘፈንህን አሰማን !»

ናስሩዲንም መላ ቅጡ የጠፋው ዜማ ማንጐራጐር ይጀምራል ።

«እንዲህ ያለችውን ጨረባ ያለ ዛሬም ሰምቼ አላውቅ» ይላል የማሳው ባለቤት ፥ በናስሩዲን ላይ እያፌዘ ።

«አይፈረድብህም ፤ አንተኮ ከዚህ አካባቢ መች ወጣ ብለህ ታውቃለህ ! እኔ አሁን ያሰማሁህ የዚህን አገር ጨረባ ዘፈን ሳይሆን የሌላ የሩቅ አገር ጨረባ ዘፈን ነው» አለ—ናስሩዲን ።

— ወፍ እንዳገርዋ ትጮሃ



# ም ስ ጢ ር

ናስሩዲን አንድ እጅግ ሲበዛ ዕውቀት የጠማው ተማሪ ነበረው ። ለሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢውን መልስ ከናስሩዲን የማግኘት ዕድል ቢሰጠውም ፣ አዕምሮው በሚያገኘው መረጃ አይረካም ነበር ። ቶሎ ተምሮ ፣ ቶሎ አውቆ ፣ እንደ መምህሩ ረቅቆ የመገኘት ፍላጐቱ ዕረፍት ይነሣዋል ።

አንድ ቀን ናስሩዲንን ፣ «መምህር ሆይ ፣ ይኽ የቁጥቁጥ ትምህርትህ ምንም አላረካኝም ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሚበቃ ትምህርት የምቀስምበትን ዘዴ ቀይስልኝ» ይለዋል ።

«ምነው ? ምን እንዲህ አስቸኰለህ ?» ይለዋል ፣ መምህር ናስሩዲን ።

«መምህር ሆይ ፤ በሕይወቴ ውስጥ ልሠራው ያቀድኩት ብዙ ነገር ስላለኝ ዕድሜዬን በትምህርት ገበታ ላይ ማገባደድ አልሻም ። የዕውቀት ምስጢር መክፈቻ ቊልፍ በእጅህ ውስጥ ናት ማለትን ስለ ሰማሁ ፣ ማወቅ የሚገባኝን በቶሎ እንዳውቅ አድር ገኝ !» ይላል ተማሪው ።

«ምስጢር ለመቀበል ዝግጁ ስትሆን ያኔ ሁሉ ንም ነገር ገልጬ እነግርሃለሁ ።»

ተማሪው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ናስሩዲንን እንደ ገና በዚሁ ጉዳይ እየጨቀጨቀ አስቸገረው ።

«ሁሉንም ነገር ባንድ ጊዜ አውቀህ ፣ የእኔን የመምህርህን አርአያ መከተል አይደል ዓላማህ ?» በማለት ናስሩዲን ነዝናዛ ተማሪውን ይጠይቀዋል ።

«አዎን ፣ መምህር !»

«ለመሆኑ የነገሩህን ምስጢር መጠበቅ ትች ላለህ ?»

«ምስጢር በመጠበቅ እንደሆን መሬት ነኝ ። እመነኝ መምህር ፤ አንዲት ቃል ለማንም ትንፍሽ አልልም !»

ናስሩዲንም ፣ «ነጋ ጠባ የዕውቀትን ምስጢር እንድገልጽልህ አላስቆም አላስቀምጥ ብለህ አስቸግ ረኸኛል ፤ አንተ ምስጢር ጠባቂ መሬት ስትሆን ናስሩዲን ምስጢር ዘክዛኪ ዘርዛራ ወንፊት ነው ብሎ የነገረህ ማነው ?» አለው ።

— ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም ።

## የማይበሉት እህል

ናስሩዲን በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ትልቅ ባሕር ዳር ቆሞ ማዕበሉ ውኃውን አረፋ እያ ስደፈቀ ፣ ከርቀት እጥመልምሎና አሽከርክሮ እያሳ በቀ በማምጣት ከዳርቻው አለት ጋር ሲያላትመው ውበቱንና ግርማውን በአንክሮ ይመለከታል ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ባሕሩ ጠጋ በማለት ውኃውን በእጁ ጨለፍ አድርጎ ቢቀምሰው ፣ ከጨዉ ኩምጣጤ የተነሣ ሆድ ውስጥ ሊገባ ቀርቶ ፣ በአፍ ለአፍታ ሊያዝ የማይቻል መሆኑ ስለ ተሰማው ፣ ይተ ፋውና ፣ «ይደንቃል ፤ ያ ሁሉ መዘናከት ፣ ያ ሁሉ ግርማ ሞገስ ፣ ባፍ እንኳን አይቀመስ !» አለ ።

— የማይበሉት እህል ከዐፈር እኩል ነው ።

# አፍና ቅብቅብ

በአንድ ወቅት ናስሩዲን በዘበኝነት ሙያ ተቀ ጥሮ መሥራት ይጀምራል ። አንድ ቀን ቀጣሪው ቤቱ ውስጥ እንደሆነ ናስሩዲንን ይጣራና ዝናብ መዝ ነብ አለመዝነቡን እንዲነግረው በመጠየቅ ፣ «ለብ ርቱ ጉዳይ ወደ ውጪ መሔድ ስለምፈልግ ልብሴ ዝናብ አይችልም» ይለዋል ።

ናስሩዲን በዘበኝነት ሥራው ስንፍና የሚታይ በት ቢሆንም ፣ ነገሮችን አገናዝቦ ከአንድ ተአማኒ ውሳኔ መድረስ ይቻላል የሚል እምነት ስለነበረው ፣ አጠገቡ ተኝታ ታንኳርፍ የነበረችው ድመት እርሱ ወዳለበት ስፍራ ስትመጣ ሰውነትዋ በውኃ ርሶ አይቶ ስለነበር ፡—

«እረ ጌታዬ ፣ ዶፉን እያወረደው ነው !» በማ ለት መልስ ይሰጣል ።

ቀጣሪውም ዝናብ የሚከላከል ልብስ ለውጦ ወጣ ሲል ፣ ዶፍ ቀርቶ ካፊያ እንዳልጣለ ይረዳል ።

ድመቷ ሰውነቷ የራሰው ዝናብ መቷት ሳይሆን ፣ ሰው ቤት ገብታ ስትንጐዳጐድ ውኃ ተቸልሶባት በመሆኑ ፣ የናስሩዲን የእንጀራው ገመድ መበጠሻ ምክንያት ሆነች ።

— አፍና ቅብቅብ ሁልጊዜ አያበላም ።



# ማልደው ቢነሡ

«ናስሩዲን ፤ አባክህ ማልደህ ከእንቅልፍህ ተነሣ !» ይለዋል አባቱ ።

«ለምን ፥ አባባ ?»

«ልጄ ፥ ማልዶ መነሣት ጥሩ ልማድ ነው ። አንድ ቀን ሰማይና ምድር ሳይላቀቅ አንድ ቦታ ስሔድ አንድ ከረጢት ሙሉ ወርቅ መንገድ ዳር ወድቆ አገኘሁ ። ማልደህ ተነሣ ልጄ ፤ ዕድልህ ምን እንደሚሰጥህ ምን ይታወቃል !»

«አንተ እኮ ያገኘኸው ከረጢት ሙሉ ወርቅ የሌሊት ገስጋሽ የጣለውን ነው እንጂ የዕድል ጉዳይ እንዳይመስልህ» አለ ናስሩዲን ።

«ልጄ ፥ የምነግርህን ስማኝ ፤ ዝም ብለህ አትከራከረኝ ! የሌሊት ገስጋሽ ይጣለው አይጣለው ማለዳ በመነሣቴ የዕድሌን አግኝቻለሁ !»

«የዕድልማ ነገር ቢሆን ኖሮ ፥ ከአንተ በፊት ማልዶ የተነሣው የሌሊት ገስጋሽ ወርቁ ለምን ይጠፋበት ነበር ?» አለ ናስሩዲን፥አባቱን ግራ በማጋባት።

— ማልደው ቢነሡ እኩሉ ቀን አይደርሱ ።

# በእንቅልፍ ይለመዳል

አንድ ጊዜ ናስሩዲን በአቅራቢያው ከሚገኘው የመቃብር ዐፀድ ውስጥ ሲንሸራሸር አንድ ነገር እግሩን ያደናቅፈውና ባዶ የመቃብር ጉድጓድ ውስጥ በጀርባው ይወድቃል ። እዚያው እወደቀበት ጉድጓድ ውስጥ እንዳለ ዓይኑን ከደን አድርጎ ሞት ስለ ተባለው ጥልቅ ምስጢር ሲያስተነትን ፣ ሸለብ ያደርገዋል ። በሕልሙም ጣዕረሞት እያንጃበበ ወደ ወደቀበት ጉድጓድ ሲመጣ ይታየዋል ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ይነቃና ከወደቀበት ጉድጓድ ተፈናጥሮ ወጥቶ የነፍስ አውጪኝ የመቃብሩን ግንብ ዘልሎ አውራ መንገድ ላይ ዱብ ሲል ፣ በመንገዱ ላይ የነበሩ የግመል ቅፍለቶች (ካራቫን) ይበረግጉና በያቅጣጫው ይበተናሉ ። የግመሎቹ ባለቤቶች ናስሩዲንን ይዘው ልቡ እስኪጠፋ ደብድበው ይለቁታል።

ናስሩዲን የሞትሞቱን ቤቱ ይደርሳል ። ሚስቱም ሁኔታውን ስታይ ምን እንደ ነካው ትጠይቀዋለች ።

«ሞቼ ፣ መቃብር ገብቼ ነበር» ይላል ናስሩዲን።

ባለቤቱም የሚቀልድባት መስሎአት ፣ «ታዲያስ ፤ ሞት እንዴት ነበር ?» ትለዋለች ።

«መጥፎ አይደለም ፤ ችግሩ ግመሎቹ እንዲበረግጉ ስታደርጊ ብቻ ነው ። ያኔ እንዳትሞቺ እንዳት ተርፊ አድርገው ይደበድቡሻል ። ከዚህ በስተቀር አይከፉም» ይላታል ፣ የፊቱን ላብ እያባበሰ ።

— ሞት በእንቅልፍ ይለመዳል ።

# ሐሳቡ ጥልቅ

አንድ ምሑር ናስሩዲንን ፣ «ለመሆኑ ዕድል ምንድን ነው ?» በማለት ይጠይቀዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «ዕድል ማለት ፣ አንዱ በሌላው ላይ ተፅእኖ ሊያደርስ የሚችል ፣ የማያቋርጥና ቊል ፍልፍ የድርጊቶች ቅደም ተከተል ነው» በማለት ይመልስለታል ።

«የሚያረካ መልስ አልሰጠኸኝም ። እኔ በመን ሥኤና በውጤት አምናለሁ» አለ ምሑሩ ።

«መልካም» አለና ናስሩዲን ፣ «ያ ከሩቅ ያለው የሰዎች ግርግርታ ይታይሃል ?» በማለት ምሑሩን ጠየቀው ።

«አዎን ፣ ይታየኛል ።»

«እንግዲያው እኔም ጥያቄ ላቅርብልህ ። ያ ሁሉ ሰው አንድ ነፍስ ገዳይ ሲሰቀል ለማየት ነው የሚተ ራመሰው ። ሰውዬው ለመሰቀል የበቃው ፣ ሰው የገ ደለበትን ጩቤ የሰጠው ሰው ስላለ ነው ? ወይስ የሰው ነፍስ ሲያጠፋ ያየ ሰው መስክሮበት ነው ? ወይስ ሰው ሊገድል ሲል ተው የሚለው ገላጋይ ሰው በማጣቱ ነው ?» አለው ።

— ሐሳቡ ጥልቅ ነገሩ ጥብቅ ።

# ዘጠኝ ሞት መጣ

ናስሩዲን በአንዲት መርከብ ብቻውን ተሳፍሮ ጥቂት ቀናት ከተጓዘ በኋላ ፣ ማዕበል ተነሥቶ መር ከብዋን ክፉኛ ግራ ቀኝ ያላጋት ጀመር ። የመርከብዋ ቆትለኛና (መሪ) ሠራተኞች መርከባቸው እንዳትሰ ጥም የተቻላቸውን ሁሉ ካደረጉ በኋላ ፣ ተስፋ በመ ቊረጥ ሁሉም በግንባራቸው ተደፍተው ከአደጋ እን ዲያድናቸው እግዜርን መለመን ያዙ ።

ናስሩዲን ግን በምንም ነገር ሳይደናገጥ አጠገ ባቸው ቁሞ ይመለከታቸው ነበር ።

የመርከብዋ መሪ ናስሩዲንን አጠገቡ በእርጋታ ቆሞ በማየቱ፣ ከተንበረከከበት ስፍራ በቊጣ ተነሥቶ፣ «መርከብዋ ፣ በውስጥዋ ያለነውም ሁሉ ልንሰጥም ተቃርበን እያየህ እንዴት ተዝናንተህ ቆመህ ትመ ለከተናለህ ?» አለው ።

ናስሩዲንም ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ ፣ «እኔ ታዲያ ምን አገባኝ ። እኔ እንደ ሆንኩ ገንዘቤን የከሰ ከስኩ ተሳፋሪ ነኝ ። የመርከብዋም ሆነ የተሳፋሪዎ ችዋ ደኅንነት አንተን እንጂ እኔን አይመለከተኝም !» አለው ።

— ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት ፣ አንዱን ግባ በለው አለ ።

# አ ደ ራ

ናስሩዲን ከአንድ የአትክልት ነጋዴ መደብር ፍራፍሬ መንትፎ ለመብላት ያስባል ። ከስፍራው እንደ ደረሰ ነጋዴው መደብሩን የሚጠብቅለት ሳተና የሆነ ቀበሮ እንዳለው በመረዳት በአቅራቢያው መንከላወስ ይጀምራል ።

ነጋዴው አንድ ቦታ ለመሔድ አስቦ ኖሮ ፣ ቀበሮውን እንዲህ ይለዋል ፤ «እኔ አንድ ቦታ ደርሼ ለመመለስ ስላሰብኩ መደብራችንን ደህና አድርገህ ጠብቅ ። አንድ ሰው በመደብራችን አካባቢ አንድ ነገር ሲያደርግ ስታይ ፣ ድርጊቱ ከመደብራችን ደኅን ነት ጋር ያለውን ግንኙነት በጥንቃቄ ማጤን አለብህ። በል አደራህን እንግዲህ ፤ ነቅተህ ጠብቅ ፤ በቶሎ እመለሳለሁ !»

ነጋዴው ለቀበሮው የሰጠውን ትእዛዝ ናስሩዲን ይሰማ ኖሮ ፣ በአካባቢው መንከላወሱን ይቀጥላል ። ቀበሮውም እንቅስቃሴውን በንቃት ይከታተላል ። በመጨረሻም ናስሩዲን በአትክልቱ መደብር ትይዩ በሚገኝ ለምለም ሣር ላይ ጋደም ብሎ ዓይኑን ይከ ድናል ። ቀበሮው ቢያይ ቢያይ ናስሩዲን ዓይኑን አይ ከፍትም ።

«መተኛት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት አይደለም ። ስለዚህ የዚህ ሰው ከመደብሩ ፊት ለፊት መተኛት ለመደብራችን ደኅንነት ጉዳት የለበትም» የሚለውን ቃል መልሶ መላልሶ ሲደጋ ግም ፣ እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ ይላል ።

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ብድግ ይልና ፣ የተኛውን ቀበሮ ተራምዶ በማለፍ ፣ ከፍራፍሬው የቻለውን ያህል በማፈስ ወደ ቤቱ ያመራል ።

— አደራ ጥብቅ ፣ ሰማይ ሩቅ ።



# አ ሳ ሳ ች

የናስሩዲን ሚስት በጣም የምትወዳት ጐረቤት ጓደኛ ነበራት ። ሚስቱ ፣ ናስሩዲን በየጊዜው እየገዛ የሚያመጣውን ሥጋ እያነሣች ትሰጣታለች ። በጉዳዩ የተቸገረው ናስሩዲንም ፣ አንድ ቀን ሚስቱን ፣ «እኔ ገዝቼ የማመጣው ሥጋ አንድ ቀንም ማዕድ ላይ ቀርቦ አይቼ የማላውቀው ለምንድን ነው ?» ብሎ ይጠይቃታል ።

«ድመቱ እየበላው ነው !» ትለዋለች ።

ናስሩዲን ከተቀመጠበት አፈፍ ብሎ ይነሣና ወደ መኝታ ቤቱ በመግባት ጐራዴውን አውጥቶ ሳሎን ቤት ከሚገኘው የዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ አስ ገብቶ በመቈለፍ የቊልፉን መክፈቻ ኪሱ ይከታል።

ባለቤቱም ፣ «ምን ማድረግህ ነው ?» አለችው ።

«ጐራዴዬን መደበቄ ነው !»

«ምን እንዳይሆን ?»

«በሁለት በሦስት ብር እየገዛሁ የማመጣውን ሥጋ በየዕለቱ እየመነተፈ መብላት የለመደ ድመት ብዙ ገንዘብ ያወጣሁበትን ጐራዴዬን አግኝቶ ይምርልኛል ብለሽ ነው ?» አላት ።

— አሳሳች ከላይ ሲሉት ከታች ።

## በሰው ቂጣ

ናስሩዲን አንድ የታመመ ወዳጁን በመጠየቅ ላይ እንዳለ ፣ የመንደሩ ሐኪም ኩትፍ ይልና ሕመምተኛውን መመርመር ይጀምራል ። ለሁለት ሦስት ደቂቃ ያህል የሕመምተኛውን ሰው ዓይን ገልጦ ፣ ጕሮሮውን አስከፍቶ ከተመለካከተና ሰውነቱን እዚህም እዚያም ከደባበሰ በኋላ ፣ «ይህንን የባቄላ እሸት አለ ልክ መብላትህን ማቆም አለብህ ። አይዞህ ምንም አትሆንም ፤ ከሁለት ሦስት ቀን በኋላ ትድናለህ» ይለውና ውልቅ ብሎ ይሔዳል ።

ናስሩዲን ሐኪሙን ተከትሎ ከቤት በመውጣት፣ «እባክህ የተከበርክ ሐኪም ፤ የወዳጄን ሕመም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እንዲህ አድርገህ ማወቅ የቻልክበትን ምስጢር ንገረኝ !» በማለት አፋጦ ይይዘዋል። ሐኪሙም ፣ «ነገሩ ይህን ያህልም ከባድ አይደለም ። ቁምነገሩ ፣ የአካባቢ ሁኔታዎችን አገናዝቦ ከአንድ ውሳኔ ላይ የመድረስ ችሎታን የሚጠይቅ ነው።ወዳጅህ ሆዱን በጣና መታመሙን ሚስቱ ነግራኝ ነበር ። ቤቱ ገብቼ አካባቢውን ስቃኝ ፣ ከሕመምተኛው አልጋ ሥር የባቄላ እንቁሪባ (ገለፈት) ተከምሮ አየሁ ። ሌላው ሳደርገው የያዝኹኝ ነገር ሁሉ ዝም ብሎ ማደናገሪያ ነው» አለው ።

ናስሩዲን ሐኪሙን ከልብ አመስግኖ ተለያዩ ።

ከዕለታት አንድ ቀን ናስሩዲን አንድ ወዳጁን ለመጕብኘት ተነሥቶ ይሔዳል ። በር በመንኳኳቱ የወዳጁ ሚስት ብቅ ስትል ናስሩዲንን ታየዋለች ።

«አንተ ነህ እንዴ ናስሩዲን ? እኔ ደግሞ ሐኪሙ የመጣ መስሎኝ... ዛሬ ሐኪም እንጂ ነገር ስንጣቂ

ፈላስፋ አያስፈልገንም ። ባለቤቴ ሆዱን በጠና አሞት በሥቃይ ላይ ነው ያለው !» ትለዋለች ።

ናስሩዲንም ፣ «ፈላስፋ ሕመም አይፈውስም ያለሽ ማነው ?» በማለት ወዳጁ ወደሚያቃስትበት ክፍል ዘው ብሎ በመግባት ፣ አካባቢውን በዓይኑ ከቃኘ በኋላ ፣ ጐንበስ ብሎ የሕመምተኛውን አልጋ ሥር ጭምር ተመለከተ ።

ከዚያም የወዳጁን ሆድ ፣ ዓይንና ግንባር በእጁ ነካ ነካ ካደረገ በኋላ ፣ ወደ ሚስቱ ዞር በማለት ፣ «አይዞሽ ምንም አይሆንም ። ከሁለት ሦስት ቀን በኋላ ድኖ ይነሣል ። አንቺ ግን ከዛሬ ጀምሮ ይህን አልጋው ሥር የከመረውን የኮርቻና የልጓም ጠፍር የመብላት ልማዱን እንዲያቆም ማድረግ አለብሽ !» በማለት ከወዳጁ ቤት ውልቅ ብሎ ወጣ ።

— በሰው ቁጣ እጅዋን ትቃጣ ።

## ያ ል ጠ ረ ጠ ረ

ናስሩዲን ከገበያ ዕቃ ገዝቶ ወደ ቤቱ የሚያደርስለት ሰው ሲፈልግ አንድ ሰውነቱ ፈርጣማ ልጅግር ተሸካሚ ከተፍ ብሎ ልሸከም ይላል ።

«መልካም ! ተሸከምና ቤቴ አድርስልኝ» ይላል ናስሩዲን ።

«በደስታ የኔ ጌታ ! ለመሆኑ ቤትዎ የት ነው ?» በማለት ይጠይቃል ዳንዴው—ተሸካሚ ።

ናስሩዲን ተሸካሚውን ከግር እስከ ራሱ በግልምጫ በመመልከት ፣ «አንት አውደልዳይ ! አንት ምሽላቃ ሌባ ! እንድትሰርቀኝ ነው ቤቴን ላንት የምጠቁመው ?» በማለት ቀልቡን ገፎ ያባርረዋል ።

— ያልጠረጠረ ተመነጠረ ።



# የደባ ገበያ

አንድ ቀን ናስሩዲን ገበያ ወጥቶ ሳለ ፣ የተለያዩ ወፎች በውድ ዋጋ ሲሸጡ ይመለከታል ። በሚቀጥ ለው የገበያ ቀን ፣ አውራ ድሮውን ይዞ ይሔድና ለሽ ያጭ ያቀርባል ። ዶሮውን ለመግዛት የጠየቀው ገበ ያተኛ ሁሉ ከአራትና ከአምስት ብር የበለጠ እንደማ ይከፈለው ይነግረዋል ።

ናስሩዲንም በአውራ ዶሮው ዋጋ መራከስ ይና ደድና ፣ «የዛሬ ሳምንት ከእኔ ዶሮ አሥር እጅ የሚያ ንሱ ወፎች እስከ ሃምሳ ብር ሲሸጡ ዋሉ ። ዛሬ ደግሞ ይህን የመሰለ አውራ ዶሮ እንዴት በአምስት ብር ሽጥልን ትሉኛላችሁ ? እንዲያው ለመሆኑ ጡር አት ፈሩም ?» ይላቸዋል ።

ከሰዎቹ መካከል አንዱ ወደ ናስሩዲን ጠጋ በማለት ፣ «ስማ ናስሩዲን ! እነዚያ በሃምሳ ብር የተ ሸጡት እኮ ዶሮዎች አይደሉም ። በቀቀን ናቸው— እንደ ሰው የሚናገሩ ወፎች !» አለው ።

«አንድ ሁለት ቃላት ከሰው አፍ ለቅመው ለሚ ቀባጥሩ ወፎች ሃምሳ ብር ትከፍላላችሁ ። የእኔ ዶሮ የሚያውቀውን ነገር ሁሉ በሆዱ አምቆ በመያዙ ዋጋውን ታራክሱታላችሁ ። ሞኛችሁን ፈልጉ ! እኔ እንደሆንኩ ዶሮዬን በርካሽ አልሸጥላችሁም !» አላቸው ።

— የደባ ገበያ ፣ በሬው ባሥር ቆዳው በሃያ ።



ናስሩዲን ለአንድ ሀብታም ጌታ ያድራል ። አንድ ቀን አሳዳሪው በዳተኝነቱ የተነሣ ፥ «ለምንድ ነው እንዲህ የምትንቀረፈፈው ? አንድን ነገር ሦስት አራቴ ካልነገርኩህ ለምንድነው የማይገባህ ? ሦስት እንቍላል ገዝተህ አምጣ ስልህ ሦስት ጊዜ ገበያ መው ጣት ትፈልጋለህ ! ለምንድነው እንዲህ አድርገህ ልቤን የምታቈስለው ?» በማለት ይጮህበታል ።

ናስሩዲን ጠባዩን ለማሻሻል ቃል በመግባት የቀጣሪውን ቍጣ እንዲበርድ ያደርጋል ።

አንድ ቀን በድንገት የናስሩዲን አሳዳሪ በጠና ይታመማል ። ናስሩዲንም በአስቸኳይ ሔዶ የመንደ ሩን ሐኪም ይዞት እንዲመጣ ይታዘዛል ።

ናስሩዲን ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ አገር ሰው አስከትሎ ይደርስና ፥ በፍጥነት ጌታው ወደ ተኛበት ክፍል በመግባት ፥ «ጌታዬ ፥ ሐኪሙንም ሌሎቹንም ይዤ መጥቻለሁ !» በማለት ያስረዳል ።

«ሌሎቹ ደግሞ እነማን ናቸው ?» ብሎ ጌታው ይጠይቀዋል ።

«ድንገት ሐኪሙ መድኃኒት ቢያዝሎት ፥ ቅጠል በጣሹንና ሥር ማሹን ፤ ስብራት ወይም ውል ቃት አለብዎት ቢባል ፥ የሰፈሩን ሁለት ወጌሾች ፤ እግዜር አይበለውና ድንገት አይተርፉም ቢባል ደግሞ ፥ ገናዡንና የሰፈር ጥሩምባ ነፊውን ይዣቸው መጥቻለሁ !» አለው ።

— ሞኝ የመከሩት ዕለት ፥ ቁንጫ የጠረጉት ዕለት (ይብሳል) ።

# የማይጽፍ ደብተራ

የናስሩዲን የመጻፍ ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ነበር ። ንባቡንም እንዲሁ ነበር የሚያልኰሰኵሰው። በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ግን እንደ ተማረ ሰው ይቈጠር ነበር ።

አንድ ቀን አንድ የሰፈሩ ሰው ለወንድሙ ደብዳቤ እንዲጽፍለት ናስሩዲንን ይለምነዋል ። ናስሩዲንም ልመናውን ለመፈጸም ይስማማና ፥ የሰውዬውን ቃል በመቀበል ደብዳቤውን ይጽፍለታል ።

ደብዳቤው ተጽፎ ከተጠናቀቀ በኋላ ፥ ሰውዬው ናስሩዲንን ፥ «በል እንግዲህ የጻፍከውን አንብብልኝ ። መልእክቴ በሙሉ በደብዳቤው ላይ መስፈሩን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ !» ይለዋል ።

ናስሩዲን ቡጭርጭር ጽሕፈቱን ለረጅም ጊዜ አፍጥጦ በመመልከት ፥ 'ውድ ወንድሜ' የሚለውን ሐረግ ሁለት ሦስቴ ደጋግሞ ካነበበ በኋላ ፥ «እረ እኔ እንጃ ፤ ከ'ውድ ወንድሜ' ቀጥሎ ያሉትን ቃላት ማንበብ አልቻልኩም !» ይለዋል ።

ሰውዬውም ፥ «ታዲያ አንተ ራስህ የጻፍከውን ማንበብ ያልቻልክ ፥ ደብዳቤው ወንድሜ ዘንድ ሲደርስ ማን ሊያነብለት ነው ?» ይለዋል—በንዴት ።

«ስማኝ ወዳጄ» አለ ናስሩዲን ፤ «እኔ ዘንድ የመጣኸው ደብዳቤ እንድጽፍልህ እንጂ እንዳነብልህ ስላልሆነ ለቀቅ አድርገኝ !»

— የማይጽፍ ደብተራ ፥ ክንፍ የሌለው አሞራ ።

# ጠይቆ መረዳት

በአንድ የትምህርት ተቋም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ናስሩዲን ዘንድ ይመጡና ንግግር እንዲያደርግላቸው ይለምኑታል ። ናስሩዲንም ልመናቸውን በመቀበል ወደ ተቋሙ ለመሔድ ከተማሪዎቹ ጋር መንገድ ይጀምራል ።

ናስሩዲን ፊቱን ወደ አህያው ጭራ አቅጣጫ በማዞር ይቀመጥና ተማሪዎቹን አስከትሎ መንገዱን ይያያዙታል ። አላፊ አግዳሚው የናስሩዲንን አህያው ላይ አቀማመጥ እያየ ፣ ግማሹም እየሣቀ ፣ ግማሹም እየተቸ ሲያልፍ የተመለከቱ ተማሪዎች በነገሩ ግራ በመጋባት ፦—

«መምህር ሆይ፤ ለመሆኑ በዚህ ዓይነት መንገድ አህያህ ላይ የተቀመጥከው ለምንድን ነው ?» ሲሉ ይጠይቁታል ።

እኔ ይህን ነገር ለምን እንዳደረግሁ ሁኔታውን ላስረዳችሁ ። ሰው ሁሉ እንደሚያደርገው አህያዬ ላይ ተቀምጬ እናንተን ከኋላዬ አስከትዬ ብሔድ ፣ ጀርባዬን ሰጥቻችሁ ስለምንጓዝ ሁኔታው ከባህላችንና ከወጋችን ውጪ ይሆናል ። እኔ አህያዬ ላይ በተለመደው መንገድ ተቀምጬ እናንተን ከፊት ባስቀድማችሁ ፣ ሁላችሁም ጀርባችሁን ስለምትሰጡኝ ከባህላችንና ከወጋችን ውጪ የመምህርነት ክብሬን ትነፍጉኛላችሁ ማለት ነው ። እንግዲህ ወጉንም ባህሉንም ጠብቀን ፣ እናንተም ከእኔ ከመምህራችሁ ኋላ ሁናችሁ ፊት ለፊት እየተያየን ለመሔድ የምንችለው በዚህ ዓይነት መንገድ አህያዬ ላይ ስቀመጥ ብቻ ነው» በማለት ናስሩዲን አስረዳቸው ።

— በጠይቆ ዕውቀት ፣ ይገኛል ክብረት ።



# ባለቤት ያከበረው

ናስሩዲን እጅግ በጣም የተዋበ ጠርቡሽ ራሱ ላይ ደፍቶ የአገሩን ንጉሥ እጅ ለመንሣት ይቀርባል ። ሥነ—ሥርዓቱ እንዳበቃ ፣ ንጉሡ በናስሩዲን ጠር ቡሽ ውበት በመማረክ ፣ «ለመሆኑ ይህን ግሩም ጠርቡሽህን ምን ያህል ገዛኸው ?» በማለት ይጠ ይቀዋል ።

«ግርማዊ ሆይ፣አንድ ሺህ ብር ነው ያወጣሁበት!»

ከአማካሪዎች መካከል አንዱ ወደ ንጉሡ ጠጋ ብሎ ፣ «አይስሙት ግርማዊ ሆይ ! ሲያብል ነው አንድ ሺህ ብር አወጣሁበት የሚለው ። አንድ ጠር ቡሽ አንድ ሺህ ብር አወጣ ሲባል ታይቶም ተሰ ምቶም አይታወቅም» በማለት ያንሾካሹካል ።

ንጉሡም ፣ «እንዴት አድርገህ ለአንድ ጠር ቡሽ አንድ ሺህ ብር ታወጣለህ ፣ ናስሩዲን ? ጠርቡሽ ሺህ ብር አወጣ ሲባል ዛሬ ገና መስማቴ ነው !» አለው ።

«እርግጥ ነው ግርማዊ ሆይ ! እኔ ለዚህ ጠርቡሽ አንድ ሺህ ብር ያወጣሁት ተርፎኝ ሳይሆን ፣ ይኸ ጠርቡሽ በዓለም ላይ ካሉት ነገሥታት በውበቱም ሆነ በግርማው ለእርስዎ ብቻ ተስማሚ መሆኑን ስላረጋገጥኩ ነው !» ይላል — ናስሩዲን ።

ንጉሡም በናስሩዲን ከንቱ ውዳሴ ልቡ በመነ ካቱ ሁለት ሺህ ብር እንዲሰጠውና ጠርቡሹን እንዲ ረከቡት ትእዛዝ ይሰጣል ።

ናስሩዲን ገንዘቡን ኪሱ ከከተተ በኋላ ፣ የጠርቡሹን ዋጋ ወደ አራከሰው አማካሪ ጠጋ ብሎ ፣ «አንተ የጠርቡሽን እርግጠኛ ዋጋ እንደምታውቅ አልጠራጠርም ። እኔ ደግሞ የንጉሦችን ደካማ ጐን ደህና አድርጌ አውቃለሁ» አለው ።

— ባለቤት ያከበረው አህያ በቅሎ ይለውጣል ።

## የጋራ ወንጋራ

ናስሩዲንና ጓደኛው ምግብ በጋራ አዝዘው ለመመገብ ወደ አንድ ምግብ ቤት ጐራ ይላሉ ። ናስሩዲን ሥጋው ቅቅል ይሁንልን ሲል ጓደኛው ደግሞ አለ ጥብስ አልበላም በማለት ድርቅ ይላል ። ሁለቱ ጓደኛሞች በዚህ ጉዳይ ሲነታረኩ ረጅም ጊዜ ያልፋል ። በመጨረሻም ናስሩዲንን ረሃብ ክፉኛ ስለ ሞረሞረው በጓደኛው ሐሳብ በመስማማት ጥብስ እንዲቀርብላቸው ያዛሉ ።

ምግቡ እስከሚመጣ በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ የናስሩዲን ጓደኛ ጠኔ ይጥለዋል ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ከተቀመጠበት ፈንጠር ብሎ ሲነሣ ያየ ሌላ ተመጋቢ ፡—

«ሐኪም ፍለጋ መሔድህ ነው ?» ይለዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «ኧረ ምን በወጣኝ ! እኔ የምሔደው ያዘዝነውን ምግብ በጥብስ ፈንታ ቅቅል እንዲያደርጉልኝ ልነግራቸው ነው !» በማለት ይመልሳል ።

# ወዳጅ ባንደበቱ

ናስሩዲን በጣም ከሚወዱት ሁለት ሴቶች መካከል አንደኛዋን መርጦ ማግባት ተስኖት ነገሩን ሲያወጣ ሲያወርድ ፣ አንድ ቀን ሁለቱም ሴቶች ከሁለት አንዳቸውን በመምረጥ ቊርጡን እንዲነግራቸው ወጥረው ይይዙታል ።

«እባካችሁ አሥሩን በመወትወት ግራ አታጋቡኝ ! የምትፈልጉትን ነገር ተጨባጭ በሆነ መንገድ በጥያቄ መልክ አቅርቡልኝና ተገቢውን መልስ እሰጣችኋለሁ» ይላል — ናስሩዲን ።

ከሁለቱ ሴቶች መካከል መልከ መልካሟና በዕድሜዋም ልጅግሯ ፣ «እሺ ፣ እኔ አንድ ጥያቄ ላቅርብልህ ። ሁለታችን አንድ ባሕር ውስጥ ገብተን ልንሰጥም ብንደርስ ማንኛችንን ቀድመህ ታድናለህ?» አለችው ።

ናስሩዲንም በዕድሜ ጠና ወዳለችው ፍቅረኛው ፊቱን አዙሮ ፣ «የእኔ እመቤት ፤ ለመሆኑ ዋና ትችያለሽ ?» አላት ።

— ወዳጅ ባንደበቱ ፣ ውሻ በጅራቱ ።



# ለቅልብልብ አማት

ሰዎች እየሮጡ ናስሩዲን ቤት ደርሰው አማቱ ድንገት ውኃ ውስጥ መግባትዋንና ቶሎ ካልደረሰ ላት ወንዙ ጠራርጎ ወስዶ ባሕር ውስጥ እንደሚጨ ምራት ይነግሩታል ። ናስሩዲንም ወደ ወንዙ በጥድ ፊያ ሔዶ ፣ ልብሱን አወላልቆ በመግባት ፣ ሽቅብ መዋኘት ይጀምራል ።

ሰዎቹም ፣ «ምን ማድረግህ ነው ፣ ናስሩዲን ? ሰውን ውኃ የሚወስደው ወደ ቁልቁል ነው ፤ እንዴት ሽቅብ ትዋኛለህ ?» እያሉ ቢጮሁበት ፤—

«ግድ የላችሁም ወዳጆቼ ፤ የአማቴን ዐመል ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ ። ሰዎች በውኃ ኃይል ቁልቁል የሚነዱ ከሆነ ፣ እርሷን መፈለጊያው አቅ ጣጫ ሽቅብ ነው !» አላቸው ናስሩዲን፣ከፈረሰኛ ውኃው ጋር እየታገለ ።

— ለቅልብልብ አማት ፣ ሚስ በትር አላት ።



# ቁርበት አንጥፉልኝ

አንድ እግር የጣለው ምሑር አንድ ሻይ ቤት ውስጥ ከተሰበሰቡ ሰዎች ጋር ሲከራከር ናስሩዲን ይደርስና ክርክሩን ራቅ ብሎ በመቀመጥ ያዳምጣል ። በምሑሩም ብልጣብልጥነት ይገረማል ።

ሻይ ቤቱ ውስጥ ምሑሩን ከብበው ከተቀመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ፣ አንድ ጠጠር ያለ ጥያቄ ይሰነዝራል ። ምሑሩም ፣ ከእጅጠባቡ ኪስ ውስጥ አንድ መጽሐፍ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ በመጠፍጠፍ ፣ «እኔ ዛሬ ላቀረብኩላችሁ ሐሳብ ምስክሬ ይኸ መጽሐፍ ነው ። መጽሐፉንም የጻፍኩት እኔ ራሴ ነኝ !» ይላቸዋል ።

ሰዎቹም ከንባብ ችሎታ አልፎ መጽሐፍ የጻፈ አዋቂ ሰው በመካከላቸው በመገኘቱ ፣ ከፍ ያለ አድናቆት የተመላበት ከበሬታ በማሳየት ፣ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ጋብዘውና በሚገባ አስተናግደው ይሸኙታል ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ናስሩዲን ወደዚያው ሻይ ቤት በመሔድ ያንን መንገደኛ ምሑር ከበው ያነጋገሩትን የሰፈሩን ሰዎች አንድ ስፍራ እጅብ ብለው ተቀምጠው የቆጥ የባጡን ሲያወሩ ያገኛቸዋል ። ናስሩዲን ቦታ ፈልጎ ከመካከላቸው ይቀመጥና አንድ ቤት ለመሸጥ ሐሳብ እንዳለው ለሰዎቹ ይነግራቸዋል ።

ከሰዎቹ መካከል አንዱ ነገሩን በማቃለል ፡—

«የምን ቤት አለህና ነው የምትሸጠው ? እንዲያው ዝም ብለህ አትቀልድብን !» ይለዋል ።

ናስሩዲን ፣ ከእጀጠባቡ ኪስ ውስጥ አንድ መልኩ የሚያምር ጡብ ያወጣና ጠረጴዛው ላይ በመጠፍጠፍ ፣ «ቤት ያለኝ ለመሆኑ ይኸ ጡብ ምስክሬ ነው። ቤቱንም የሠራሁት እኔ ራሴ ነኝ!» አሳቻው።

— ጅብ አያውቁት አገር ሔዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ።

## ቀን አያውቁ

ናስሩዲንና አንድ ሰውዬ መንገድ ላይ ይገናኛሉ። ሰውዬው ለናስሩዲን የእግዜር ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ፣ «እባክህ ዛሬ ከሣምንቱ የትኛው ቀን እንደሆነ ብትነግረኝ» በማለት ይጠይቀዋል ።

ናስሩዲንም ፣ «በእውነቱ ልነግርህ አልችልም ፤ እኔም ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ነኝ ። በዚህ አገር ሥርዓትና ደንብ የዛሬው ቀን ማን እንደሚባል አላውቅም» አለው ።

# ደስታና መከራ

አንድ ሰውዬ በኀዘንና በትካዜ ተጨብጦ መን ገድ ዳር ተቀምጦ ሳለ ናስሩዲን ጠጋ ብሎ ምን ችግር እንዳጋጠመው ይጠይቀዋል ።

ሰውዬውም ፤ «ወዳጄ ሆይ ፤ እኔ ለሕይወት ዘመኔ በሙሉ በቅቶ የሚተርፍ ሀብትና ንብረት አለኝ ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ስኖር አንድም ቀን ደስ ብሎኝ አያውቅም ። አሁንም ቤትና ንብረቴን ትቼ ደስታ የሚገኝበት ስፍራ እንዳለ በማለት በያለበት በመንከራተት ላይ እገኛለሁ ። ሆኖም እስካሁን ደስ የሚያሰኝ ነገር አላጋጠመኝም» በማለት ያዋየዋል ።

ናስሩዲን ምንም ቃል ሳይተነፍስ የሰውዬውን የመንገድ ቦርሳ መንትፎ ይፈተለካል ። ሰውዬው ከተ ቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሥቶ ናስሩዲንን መከታ ተል ይጀምራል። ናስሩዲን አካባቢውን ደህና አድርጎ ያውቅ ስለነበር ፤ መንገድ እያሰባበረ በመሮጥ ከሰው ዬው ለመራቅ አላስቸገረውም ። ሰውዬውም ናስሩዲን የገባበትን አቅጣጫ በመከተል ላቡ እስከሚንጠፈ ጠፍ መሮጡን ቀጠለ ። በመጨረሻም ናስሩዲን ይሽ ሎከለክባቸው ከነበሩት አቋራጭ መንገዶች ወጥቶ አውራ ጐዳና ላይ ሲደርስ ፤ ከሰውዬው የመነተፈውን ቦርሳ መንገድ ዳር አስቀምጦ እርሱ በአቅራቢያው ሠወር ብሎ ይጠባበቅ ጀመር ።

ሰውዬው በንዴት ጠጉሩን እየነጨ ከአውራው መንገድ በሩጫ ደረሰ ። ቦርሳውን አውራው መንገድ ዳር ተቀምጦ ሲያይ ፤ ከደስታው ብዛት እጁን ወደ



ሰማይ እያርገበገበ በመድረስ ፣ ቦርሳውን ማግኘቱ እውነት አልመሰለህ ብሎት ፣ ከመሬት ላይ አንሥቶ እቅፍ አደረገው ።

ናስሩዲንም ከተደበቀበት ስፍራ ሆኖ ፣ «ጅሎ ፤ ደስታ ይሉሃል ይኸው ነው !» አለ ።

— ደስታና መከራ ከቀኝና ከግራ ።

# መብልን ከሰው ቤት

ናስሩዲን አገር ለመጐብኘት አንድ ተማሪውን አስከትሎ ሲዘዋወር ፣ በደረሱበት ስፍራ ሁሉ ደህና ቤት እየመረጡ ሲለምኑ ፣ ምግብም መጠጥም እንደ ልብ ያገኙ ነበር ። ናስሩዲን ምግቡን በላልቶ ፣ መጠጡን ተጐንጭቶ ሲያበቃ ፣ እዚያው እተቀመጠበት ስፍራ ላይ እንቅልፍ ይዞት ጥርግ ይል ነበር ። ተማሪው በበኩሉ ከምግቡ በላ በላ ፣ ከመጠጡም ጠጣ ጠጣ ያደርግና ተነሥቶ በመቆም ሰውነቱን ለጥቂት ጊዜ አርገፍግፎ እንደገና ምግቡንና መጠጡን ይያያዘዋል ።

አንድ ቀን ናስሩዲን የተማሪውን የአበላል ፈሊጥ ከተመለከተ በኋላ ፣ ለምን ከተለመደው ሥርዓትና ወጣ ውጪ እንደሚመገብ ይጠይቀዋል ።

ተማሪውም ፣ «መምህር ሆይ ፤ እንዲህ እንዳየ ኸኝ የምመገብበት ምስጢሩ ወዲህ ነው ። በመጠኑ ተመግቤ ፣ በላዩ ላይ የሚጠጣ ነገር ቸልሼበት ፣ ከዚያም ቆሜ በመንጠራራት ሰውነቴን ሳርገፈግ ፈው ፣ ምግቡ ሆዴ ውስጥ ቦታ ቦታውን ይይዛል ። እንዲህ እያደረግሁ ያለ ምንም ችግር ብዙ መብላት እችላለሁ» አለው ።

ናስሩዲንም ያንድ እግር ጫማውን አውልቆ ተማሪው ጭንቅላት ላይ ሁለት ሦስት ጊዜ ካሳረፈበት በኋላ ፣ «ይህን የመሰለ ጠቃሚ ምስጢር ከእኔ ከመም ህርህ እንዴት አድርገህ ትሠወራለህ ? ያንተን አባ ላል ዘዴ አውቄ ቢሆን ኖሮ ፣ እስከ ዛሬ በየሰዉ ቤት ጠግብኩ እያልኩ የመለስኩት ያ ሁሉ ምግብ አያመ ልጠኝም ነበር።በጣም ነው ጉድ የሠራኸኝ !» አለው።

— መብል ከሰው ቤት መኝታን ከቤት ።

## ያ ል ተ ነ ካ

በአንድ አሳቻ መንገድ ላይ አንድ ኪስ አውላቂ ናስሩዲንን ያገኘውና ቦርሳውን ለመንጠቅ ይሞክ ራል ። ናስሩዲን በጊዜ ነቅቶ ስለነበር ከሌባው ጋር ግብግብ ይገጥማል ። ከብዙ ትግልና ትንቅንቅ በኋላ ፣ ናስሩዲን ሌባውን መሬት ላይ ጥሎ አንድ ሁለቴ እን ዳቀመሰው ፣ አንዲት ሴት በዚያ በኩል ስታልፍ ታያቸዋለች ።

ቆም ብላ ሁኔታውን ከተመለከተች በኋላ ፣ «አንተ ጨካኝ ወንበዴ ! እንዴት ብትጠግብ ነው ይህን እኩያህ ያልሆነውን ሰው መሬት ላይ ጥለህ ባልተወለደ አንጀትህ እንዲህ የምትነርተው ! በል አሁን ፈጥነህ ተነሥ !» ትለዋለች ።

ናስሩዲንም ፣ «የኔ እመቤት ፤ ይህን ቀማኛ ኪስ አውላቂ ለመጣል የደረሰብኝን ሥቃይ ቢያዩ ኖሮ እንዲህ ባልፈረዱብኝ ነበር !» አላት ።

— ያልተነካ ግልግል ያውቃል ።

# የውኃ መጥለቅለቅ

ናስሩዲንና አንድ ገበሬ መንገድ ላይ ይገናኛሉ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ገበሬው ፣ ዘንድሮ መንግሥት ከፍ ያለ ውለታ ነው የሠራልኝ ። እርሻዬ በውኃ ከመጥለቅለቁ የተነሣ የዘራሁት ሁሉ መሬት ገብቶ በመቅረቱ ፣ እስከሚቀጥለው ዓመት የሚያቆየኝ መደጐሚያ ገንዘብ ተሰጠኝ» አለ ።

ናስሩዲን የሰማውን ነገር ለጥቂት ጊዜ በአዕምሮው ውስጥ ካሰላሰለ በኋላ ፣ «እረ እባክህ ፣ አንድን ማሳ እንዴት አድርጎ በውኃ ማጥለቅለቅ እንደሚቻል ምስጢሩን ለኔም ብትነግረኝ!» አለው ።

# እንጀራ ቢያዩት

የባግዳዱ ካሊፍ ሦስት ሺህ ለሚሆኑ የከተማዋ ታዋቂ ሰዎች ታላቅ ግብር ባዘጋጀበት በዓል ላይ ናስሩዲን ሳይጠራ ገብቶ ከእንግዶቹ ጋር ተቀላቅሎ ይቀመጣል ። የካሊፉ ዓመታዊ ግብር በዝግጅቱም ሆነ በምግቡ ዓይነት ይኸ ቀረሽ የማይባል ነበር ። ናስሩዲን ይህን ዝናው ከአጽናፍ አጽናፍ የሚወራለ ትን ድግስ ለመኰምኰም በመቋመጥ ይጠባበቅ ነበር ።

የሙዚቃውና የውዝዋዜው ሥነ-ሥርዓት ለረ ጅም ጊዜ ተካሔዶ ካበቃ በኋላ ፥ ዝርግ የሆን ከወርቅ የተሠራ ሣህን የያዙ አሳላፊዎች ተግተል ትለው በመግባት ፥ አምስት አምስት ሆነው በተቀ መጡት እንግዶች ጠረጴዛ ላይ አኖሩት ። ጅራትዋን እንደ ጃንጥላ የዘረጋችና አስደናቂ በሆነ ጥበብና ጥንቃቄ ተውባ የተጠበሰች ጣዎስ (ፒኮክ) በሣህኑ መካከል ቆማ ትታያለች ።

እንግዶቹ በሙሉ ከፊታቸው በቀረበችው ጣዎስ አጠባበስ ጥበብና ውበት በመመሰጥ አፋቸውን ከፍተው ፥ ዓይናቸውን አፍጠው በመመልከት ብቻ ብዙ ጊዜ አለፈ ። ማንም የቀረበለትን ምግብ እጁን ዘርግቶ ለመንካት የደፈረ አልነበረም ።

ናስሩዲን ግን ነገሩ አላማረውም ። ረሃብም ሆዱን እየሞረመረው ተቸግሯል ። ቢያይ ፥ አሠራሩን ከማድነቅ በቀር ምግቡ አይበላም ። ናስሩዲን ከተቀ መጠበት ብድግ ብሎ ፥ «እርግጥ ! ይኸ አሁን ማዕዳችን ላይ የቀረበው ምግብ ሲያዩት ያምራል ! ያስጐመ ጃል ። ታዲያ እንዲሁ እያየነውና እየቋመጥን በረ ሃብ ከምናልቅ በልተነው ብናርፍ አይሻልም!?» አለ ፥ ዓይኑን አፍጥጦ ።

— እንጀራ ቢያዩት አያጠግብም ።

# ገበያ ቢመቻት

ናስሩዲን ተቀጥሮ ይሠራበት የነበረውን ሻይ ቤት የአገሩ ንጉሥ እግረ መንገዱን በአካባቢው ሲያ ልፍ ይጐበኘዋል ። ንጉሡና አጃቢዎቹ ሻይና እንቍ ላል ጥብስ አዝዘው በሚገባ ይስተናገዳሉ ።

በልተው ካበቁ በኋላ የሻይውንና የእንቍላሉን ጥብስ ዋጋ እንዲነግራቸው ናስሩዲንን ይጠይቁታል ።

«ግርማዊነትዎና አምስት አጃቢዎችዎ ለተመ ገባችሁት የእንቍላል ጥብስና ሻይ አንድ ሺህ ብር ያስከፍላችኋል» ይላል ናስሩዲን ።

«እዚህ አገር እንቍላል ብርቅ መሆን አለበት ። ለምንድን ነው ምግባችሁ እንዲህ ውድ የሆነው ?» በማለት ንጉሡ ይጠይቃል ።

ናስሩዲንም ፥ «ግርማዊ ሆይ ! በዚህ አካባቢ ውዱና ብርቁ የእንቍላሉና የሻይው ዋጋ ሳይሆን የርስዎ ጕብኝት ነው !» አለ ።

— ገበያ ቢመቻት ልጅዋን ሸጠቻት ።



# ማቅ ይሞቃል

ናስሩዲን አንድ ምሽት ላይ እየተዘዋወረ ሲን ሸራሸር ከአንድ በግንብ ከታጠረ ትልቅ ግቢ ይደር ሳል ። ግቢው ውስጥ ምን እንዳለ ለማየት ግንቡ ላይ ተንጣልሎ እንደ ወጣ ፣ ካንዲት ውብ ከሆነች ኮረዳ ጋር ጭራቅ የመሰለ የሚያስፈራ ፍጥረት ሲዳራ ይመ ለከታል ። ናስሩዲን ግንቡን ዘሎ በመግባት ያንን አስቀያሚና አስደንጋጭ ፍጥረት በዱላና በጩኸት አዋክቦ ከግቢው ድራሹን ያጠፋዋል ። ተልእኮውን ፈጽሞ ከቆንጆዋ ልጅ የምስጋና ቃል ለመቀበል መለስ ሲል ፣ ልጅቱ ሁለት ጊዜ በጥፊ ትወለውለዋ ለች።ሁለት ጠብደል አሽከሮችዋም ናስሩዲንን ብብቱ ሥር ሰቅስቀው በመያዝ ከግንቡ አሻግረው መን ገድ ላይ ይወረውሩትና ከወደቀበት ቦታ ላይ እንዳይ ሞት እንዳይሽር አድርገው ይረጋግጡታል ።

ናስሩዲን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነፍሱን እንደ ዘራ ፣ ያቺ ውብ ልጅ የዚያን አስቀያሚ ፍቅረኛዋን ስም እየጠራች ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ይሰማታል ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ፣ «ሞኝና ተላላው እኔ ነኝ ። 'ሰውን ደስ የሚያሰኘውን ጣዕም ለይቶ ማወቅ አይቻልም' የሚባለው እውነት ነው ለካ» አለ ።

— ማቅ ይሞቃል ፤ ሻሽ ይደምቃል ፤ ገቢውን ባለቤቱ ያውቃል ።

ያገሩ ንጉሥ አሽከሮቹን አስከትሎ ለአደን ሲወጣ ፣ ናስሩዲንን ከሩቅ ያየዋል ። ከአሽከሮቹ አንዱን ይጠራና ፣ «ወደ አደን ሲወጣ ሙላ (አለቃ) ማየት አጉል ገድ ስለሆነ ፣ ናስሩዲን እኔ አቅራቢያ ከመድረሱ በፊት የምታደርጉትን አድርጋችሁ ወዲያ አባርልኝ! » ይለዋል ።

አሽከርየውም ሮጦ ሔዶ ናስሩዲንን በመያዝ አንድ ሁለቴ ጐሻሽሞ ያባርረዋል ።

ንጉሡ ከወትሮው የተሻለ አደኑ ይቀናውና ይመለሳል ። ቤተ መንግሥቱ ከገባ በኋላ ናስሩዲን ተጠርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ይሰጣል ።

«ዛሬ ጠዋት በደረሰብህ ነገር በጣም አዝናለሁ ፣ ናስሩዲን! በሩቅ ሳይህ ገደ ቢስ መስለኸኝ ፈርቼ ነበር። ገድህ ስላማረ ፣ አደኑ ካሰብኩት በላይ ቀንቶኝ ነው የተመለስኩት!» አለው ።

ናስሩዲንም ፣ «ግርማዊ ሆይ ! እርስዎ ጠዋት እኔን አይተው አደኑ ቀንቶዎት ተመለሱ ። እኔ ደግሞ እርስዎን በማየቴ ዱላ ቀመስኩ ። ታዲያ ገደ ቢሱ ማን ይመስልዎታል?» አለ ።

# አልቆልኝ ነበር

ናስሩዲን ጓሮው ካጸደቃቸው የአትክልት ዓይነቶች መካከል መርጦ ለንጉሡ ገጸ-በረከት ለማቅረብ በማሰብ ፥ ትልቅ ዱባ መርጦ ይዞ ሲሔድ መንገድ ላይ አንድ የሚያውቀው ሰው ያገኘዋል ። ሰውዬው የናስሩዲንን ሐሳብ ከተረዳ በኋላ ፦

«አብደሃል እንዴ ፥ ናስሩዲን! ለንጉሥ ቀርቶ ለአንድ ትልቅ ሰው እንኳን ዱባ በገጸ—በረከትነት ቀርቦ አያውቅም ። ንጉሥ ፊት የበለስ ፍሬ ወይም የወይን ዘለላ ይዘህ መቅረብ አለብህ» ይለዋል ።

ናስሩዲን የሰውዬውን ምክር በመቀበል የወይን ዘለላ ገዝቶ ንጉሡ ዘንድ ይዞ ይቀርባል ። ንጉሡም የመጣለትን ገጸ—በረከት በደስታ ተቀብሎ ናስሩዲንን ሸልሞ ያሰናብተዋል ።

ናስሩዲን ጥቂት ጊዜ ሰነባብቶ ፥ በርካታ የሚያማምሩ የብርቱካን ፍሬዎች ገዝቶ ለንጉሡ ገጸ-በረከት ያቀርባል ። ንጉሡ በዕለቱ በሆነ ነገር ተበሳጭቶ ስለነበር ፥ የብርቱካኑን ፍሬ አንድ በአንድ እያነሣ በመወርወር ናስሩዲን ላይ ይፈጠፍጠው ጀመር ። ናስሩዲን የሚበቃውን ያህል የብርቱካን ፍሬ ውርጅብኝ ከቀመሰ በኋላ የነፍስ አውጭኝ ሮጦ ያመልጣል ።

ወደ ቤቱ በማዝገም ላይ እንዳለ ፥ «ለካስ ሰዎች ትንንሽ ነገሮችን ገጸ—በረከት የሚያቀርቡት ቢወረወርባቸውም እንደማይጐዳቸው አውቀው ለብልሃታቸው ነው ። ዛሬ ያንን ዱባ አቅርቤ ቢሆን ኖሮ አልቆልኝ ነበር ! » አለ ።

## ባፍንጫዬ ይውጣ

ናስሩዲን የሚኖርባትን መንደር አቋርጦ የሚያ ያልፍ አንድ ትልቅ አውራ ጐዳና ሥራው ተጠናቅቆ አገልግሎት ላይ ውሎ ነበር ። አንድ ቀን ናስሩዲን አውራ ጐዳናውን ለማየት በማሳብ ማልዶ በእግሩ ጉዞ ጀመረ ። የአውራ ጐዳናውን አሠራርና ውበት እያደነቀ ረጅም ርቀት ከሔደ በኋላ ፣ ስለ ደከመው ከመንገዱ ዳር ከሚገኝ አንድ ዛፍ ሥር ጢጋ ብሎ በመ ቀመጥ ዕረፍት በማድረግ ላይ እንዳለ ፣ እንቅልፍ ሸለብ አደረገው ። ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ሲነቃ ፣ ጠርቡሹ ከራሱ ላይ የተወሰደበት መሆኑን ተገነዘበ ። ከዚያም በደረሰበት ሁኔታ እየተበሳጨ ወደ ስፈሩ ተመለሰ ።

በማግሥቱ የጠርቡሹን ሌባ ለማፈላለግ ማልዶ በመነሣት በአዲሱ አውራ ጐዳና ላይ እስከ ቀትር ሲጓዝ ከቆየ በኋላ ፣ ስለ ደከመው ጥቂት አረፍ ለማለት የመንገዱን ጥግ ይዞ ተቀመጠ ። ጥቂት ጊዜ እንዳረፈ አሁንም እንቅልፍ ሸለብ አደረገው ። ወዲያው የብዙ ሰዎች ድምፅ በመስማቱ ከእንቅልፉ ነቃ ። ናስሩዲን ከሰዎቹ መካከል ወደ አንዱ ጢጋ ብሎ ፣ የግርግሩን ምክንያት ቢጠይቀው ፣ የአዲሱን አውራ ጐዳና ደኅንነት በኃላፊነት እንዲያስጠብቅ የተመደበው የዘብ አለቃ ፣ መንገድ ዳር ተኝቶ በመገኘቱ አንገቱ ወደ ሚቀላበት ስፍራ በመውሰድ ላይ መሆኑን አስረዳው ።

ናስሩዲንም ሰውዬውን ፣ «በል በቃኝ ወንድሜ! እዚህ አውራ ጐዳና ላይ የሚተኛ ፣ ወይ ንብረቱን ወይ አንገቱን የሚያጣ ከሆነ ባይታይ ባፍንጫዬ ይውጣ!» አለው ።

# ከመሞት መሰንበት

ናስሩዲን አንድ በረሃ አቋርጦ ሲጓዝ ሦስት የሚ ያስፈሩ ሰዎች አንድ ቁጥቋጦ ሥር ተቀምጠው ሲጨ ቃጨቁ በአጠገባቸው ያልፋል ። ከሦስቱ አንዱ ናስሩዲንን ይጠራውና ፡—

«የመስጊድ ሕንፃ አመጣጥ እንዴት እንደሆነ ሦስታችንም ሦስት የተለያዩ ሐሳቦች አቅርበን መስ ማማት አልቻልንም ። እባክህ ገላግለን» ይለዋል ።

«ሐሳባችሁን ሳላውቀው እንዴት መፍረድ እች ላለሁ ?» ይላቸዋል — ናስሩዲን ።

«ከሰማይ ነው የወረደው !» አለ አንደኛው ።

«ከባሕር ውስጥ ነው የወጣው ! » አለ ሁለተኛው ።

«እንደ ቁልቋል ነው የበቀለው!» አለ ሦስተኛው።

ሦስቱም ሰዎች ሐሳባቸውን ሲያቀርቡ ጩቤአ ቸውን መዝዘው የማስፈራራት እንቅስቃሴ በማሳየት ነበር ።

ናስሩዲንም ፣ «ሦስታችሁም ተሳስታችኋል ! የመስጊድ ሕንፃ የተሠራው በእጃቸው ሰማይን መዳ ሰስ በሚችሉ በጥንት ዘመን ይኖሩ በነበሩ ግዙፍ ሰዎች ነው !» ብሏቸው እግሬ አውጪኝ አለ።



## ፈሪ ለናቱ

አንድ በጭካኔው የታወቀ የሽፍቶች አለቃ ናስሩዲንን ጠብቆ ይይዘውና ፣ «ዝናህን እንደ ሰማ ሁት ብዙ ምስጢር ፣ ብዙ ብልሃት ታውቃለህ ይባላል ። በል እንግዲህ በነዚህ ጭፍሮቼ ፊት የምታውቀውን ነገር ሳትደብቅ ንገረኝ ። አለበለዚያ እዚያ በምታየው ዛፍ ላይ እንጠለጥልሃለሁ !» አለው ።

ናስሩዲን ምንም ሳያመነታ ፣ «ጌታዬ ብዙ ድንቅ ነገር እየታየኝ ነው! ከሰማየ ሰማያት አንድ ግዙፍ የሆነ ጀፌ አሞራ እየከነፈ ሲወርድ ፣ ከምድር ማኅፀን ውስጥ መናፍስት እየተተራመሱ ሲወጡ ሲታገሉ ይታየኛል!» አለ ።

የሽፍቶቹ አለቃም ፣ «ከሰማይ ርቀት ከምድር ጥልቀት ይኸ ሁሉ ነገር በምን ተአምር ሊታይህ ቻለ?» ይላል ።

ናስሩዲንም ፣ «በፍርሐት ተአምር ፣ ጌታዬ! የፍርሐት ተአምር ነው ይህን ሁሉ ድንቅ ነገር የሚያሳየኝ» አለው ።

— ፈሪ የናቱ ልጅ ነው ።



# ፊት ያሞጠሙጢል

ታርታሮች ምዕራብ እስያን በወረራ ባጥለቀለቁ በት ወቅት ፣ ናስሩዲን በአንድ መስጊድ ውስጥ ለተ ሰበሰቡ አማኞች ስብከት ያሰማ ነበር ። ስብከቱም በታ ርታሮች መሪ በታሜርሌን ላይ ያለውን ጥላቻና ተቃውሞ በግልጽ የሚያንጸባርቅ እንደነበረ ለአድ ማጮች ሥውር አልነበረም ።

ታሜርሌን ቀደም ብሎ ናስሩዲን በእርሱ ላይ የነበረውን ጥላቻ ያውቅ ስለነበር ፣ አልባሌ ሰው በመምሰል የደርቡሽ ልብስ ለብሶ ከጥቂት ጭፍሮቹ ጋር መስጊዱ ውስጥ ገብቶ ስብከቱን ያዳ ምጥ ነበር ።

ናስሩዲንም ስብከቱን ፣ «እነዚህን አረመኔና የሰው አገር ከመውረር ሌላ ሥራ የሌላቸውን ታር ታሮች እግዜር ዶግ አመድ ያደርጋቸዋል!» በማለት ደመደመ ።

«እግዜር እርግማንህን አይሰማልህም!» አለ ፣ ሕዝቡ መካከል ተቀምጦ የነበረ ሰውዬ ፣ ከመቀመ ጫው አፈፍ ብሎ በመነሣት ።

«ለምን አይሰማኝም?» አለ ናስሩዲን ።

«እናንተ ለፈጸማችሁት መጥፎ ሥራም ሆነ ሳትፈጽሙት ለቀራችሁት በጎ ተግባር ተገቢ ፍዳ ችሁን መቀበል አለባችሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ የመ ንሥኤና የውጤትን ሕግ መዘንጋት የለብህም ።እና ንተ ቅጣት የሚገባችሁ መሆኑ ከታወቀ ፣ ያ እናንተን እንዲቀጣ የተላከባችሁ ቀጪ ፣ ቅጣት ይደርስበታል

ብሎ ማመን እንዲያው ከንቱ ድካም ነው!» አለ ሰውዬው ።

የደርቡሹ መልስ የዋዛ አልነበረም ። ናስሩዲንም ሁኔታውን በመረዳት ንግግር ያደርግበት በነበረው መድረክ ላይ እየተንጐራደደ ፥—

«ለመሆኑ አንተ ማነህ? ስምህስ ማን ይባላል?» በማለት ማስፈራራት እየቃጣው ጠየቀ ።

«እኔ ደርቡሽ ነኝ።ስሜም ቲሙር ይባላል» አለ ።

በዚህ ጊዜ የታሜርሌን ጭፍሮች ከተቀመጡበት ስፍራ ብድግ ብድግ በማለት ደብቀው ያስገቡትን ቀስታቸውን ወጥረው ይዘው ቆሙ ። ናስሩዲንም ዙሪያ ገባውን በዓይኑ ገረፍ በማድረግ የሁኔታውን አደገኛነት ማጤን ቻለ ።

«እንዲያው ለማወቅ ያህል፥የስምህ መጨረሻው «ሌን» ነው?» አለ ናስሩዲን ፥ ሲፈራ ሲቸር ።

«አዎን ፥ አንደኛው ስሜ ታሜርሌን ነው!» በማለት ደርቡሹ መልስ ሰጠ ።

ናስሩዲን በፍርሐት ተውጠው ወደ ተቀመጡት ተሰብሳቢዎች ፊቱን በማዞር ፥ «ወንድሞቼ ሆይ ፥ እስካሁን መደበኛውን ጸሎት ስናደርስ ቆይተናል ። ከአሁን በኋላ ደግሞ የጸሎተ—ፍትሐታችንን ሥነ-ሥርዓት እንጀምራለን!» አለ ።

ናስሩዲን በዚህ ንግግሩ የታሜርሌንን ወዳጅነት ለማፍራት በቅቷል ይባላል ።

— ፊት ያሞጠሙጢል ፤ በኋላ ያፈጢል ።

# ያመኑት ፈረስ

ናስሩዲን ከሰዎች ጋር ተቀምጦ ሲያወራ የሚከተለውን ቃል ተናገረ ፤—

«አንድ ጊዜ አንድ በጣም የታወቀ ታላቅ ሰው ቤት ሔጄ ፥ ከብዙ ሰዎች ጋር ሆነን ፈረሶቹን አንድ ባንድ ሲያስጎበኘን ፥ ከፈረሶቹ መካከል አንዱን ፥ 'ይህንን አጥባቂ ፈረሴን እስከ ዛሬ ድረስ ጋልቦ የሚገራልኝ ሰው ጨርሶ ማግኘት አልቻልኩም' አለን ። እኔም ከሰዎቹ መካከል ድምፄን ከፍ አድርጌ፥ 'ይህን የመሰለ ድንጉላ ፈረስ እንዴት የሚጋልበው ሰው ታጣ ይባላል? በሺህ የምንቈጠር ፈረስ ጋላቢዎች ፥ ጉግስ ተጫዋቾች ባለንበት አገር እንዴት እንዲህ ይባላል?' በማለት ፥ እኔነቴን ሁሉም እንዲያውቁት ከእንግዶቹ ፊት ቀድሜ ወጣሁ!»

ከናስሩዲን ጋር ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ ፥ «መጨረሻውስ ምን ሆነ?» በማለት ጠየቀ ።

«አፍታ ሳልቆይ ከመሬት ጋር አደባልቆ አሳረፈኝ!» አለ ናስሩዲን ።

— ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ ።



# የማይሆን ነገር

ባንድ በጣም በሚውብቅ ከቀትር በኋላ ፣ ናስሩ ዲን ነፋስ ለመቀበል በመንሸራሸር ላይ እያለ ፣ ምራቅ የሚያስውጥ በሳል የወይን ዘለላ በእቅፉ ይዞ የሚሔድ ሰው አጋጠመው ። ናስሩዲን ሰውዬውን በከንቱ ውዳሴ ደልሎ ከያዘው የወይን ዘለላ እንዲያ በላው በማሰብ ለጥ ብሎ እጅ በመንሣት ተጠጋው ።

«መምህር! እባክዎን ከያዙት ወይን ያቅምሱኝ!» አለው ናስሩዲን ።

«እኔ መምህር አይደለሁም!» አለ ሰውዬው ፣ የናስሩዲን ከንቱ ውዳሴ ስላልጣመው ።

«አለቃዬ! እንዲያው ከወይኑ ያቅምሱኝ!»

«ሰውዬው! እኔ አለቃም አይደለሁም!»

«ክቡር ጌታዬ! ዓይኔን ጥዬበታለሁና ከያዙት ወይን አንድ ሁለት ፍሬ እንኳን አይንፈጉኝ!» አለ ናስሩዲን ፣ ሰውዬውን በከፍተኛ የክብር ስም ለመሸ ንገል እየሞከረ ።

«ምነው ተወት ብታደርገኝ! እኔ 'ክቡርም ፣ ጌታም' አይደለሁም!» በማለት ሰውዬው ናስሩዲን ላይ ጮኸበት ።

በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ፣ «እንግዲያው በፈጠረህ ማንነትህን እንዳትነግረኝ ፤ ማንነትህን ከነገርከኝ በኋላ ደግሞ ፣ የያዝኩት የወይን ዘለላ አይደለም ማለ ትህ እንደማይቀር ገብቶኛል!» አለው ።

— የማይሆን ነገር የገለቢጦሽ ፣ ያንቺን ላንቺ ማን አለሽ ?

# ሰማይ ቢያኩ

ናስሩዲን አንድ የፍልስፍና ምሑር መንገድ ላይ ይገናኛሉ ። ፈላስፋው የናስሩዲንን ውስጣዊ ግንዛቤ ለመፈተን በማለት ፥ ወደ ሰማይ አንጋጥጦ እየተመ ለከተ እጁን አየር ላይ አወዛውዞ አንድ ዓይነት ምል ክት ያሳየዋል ።

ፈላስፋው አየር ላይ ያሳየው ምልክት ፥ «ማን ኛውንም ነገር አካትቶ የሚይዝ አንድ እውነታ ብቻ አለ» የሚል ትርጕም ነበረው ።

ከናስሩዲን ጋር አብሮ የነበረ አንድ ያልተማረ ባላገር ሰው ፥ ፈላስፋው እጁን ሰማይ ላይ ሲያወራጭ እንዳየ ፥ «ጠንቀቅ ማለት ይሻላል ! ሰውዬው ንክ ሳይሆን አይቀርም !» በማለት ፥ ራሱ ተጠንቅቆ የናስ ሩዲንን ምላሽ ለማየት ነቅቶ ይጠብቅ ነበር ።

ናስሩዲን ከያዘው ኮረጆ ውስጥ አንድ ገመድ አውጥቶ ለጓደኛው አቀበለው ። ጓደኛውም ፥ «መል ካም ፥ ሰውዬው ነገር ካመጣ በዚህ ገመድ እንጠፍረ ዋለን!» በማለት በልቡ አሰበ ።

ፈላስፋው ግን ፥ የናስሩዲንን ለጓደኛው ገመዱን መስጠት የተገነዘበው ፥ «አብዛኛው ሰው ከእውነት ለመድረስ የሚያደርገው ጥረት ሰማይ ላይ በገመድ ተንጠላጥሎ እንደ መውጣት ያህል ነው» ከሚለው ትርጕም አንጻር ነበር ።

— ሰማይ ቢያኩ ፥ ጤፍ ቢለኩ ።

# መንገድ ሳለ በዱር

ናስሩዲን ከሔደበት ስፍራ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ነበር ። አካባቢው በፀሐይዋ ብርሃን የደመቀበት ፣ የዙሪያ ገባው ልምላሜ ዓይን የሚማርክበት ወቅት ነበር ።

ናስሩዲንም ባጋጣሚው ቀልቡ በመማረኩ ፣ «ይህን በመሰለ ደስ የሚል ቀን በዚህ ወጣ ገባና አቧራማ መንገድ ላይ በመዳከር ምን አደከመኝ ። በዚያ ልምላሜው በሚያጓጓው ደን ውስጥ አሰባብሬ ብሔድ በወፎች ዜማ፥ በአበቦች ውበትና ሽታ፥ በአየሩ ሽውሽውታ እየተደሰትኩ ቤቴ መግባት እችላለሁ!» በማለት ወደ አቅራቢያው ደን ጐራ አለ ። ጥቂት ጊዜ እንደ ሔደም ፣ ድንገት ሳያስበው ሣር የለበሰ ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ ።

ናስሩዲን ጉድጓዱ ውስጥ ተንጋሎ እንዳለ ፣ «መቼም እንዳሰቡት አይሆን ! እንዲያው ለመሆኑ በዚህ በውብ ደን በተሸፈነ ፣ ዓይን በሚማርክ አካባቢ እንዲህ ያለው ውድቀት ያጋጠመኝ ፣ በዚያ አቧራማና ገላጣ መንገድ ላይ ብጓዝ ኖሮ ምን ዓይነት አደጋ በደረሰብኝ ነበር!» በማለት ራሱን አጽናና ።

— መንገድ ሳለ ብዱር ፤ በቅሎ ሳለ በእግር ።



# ፈሪ በገዛ ጠቡ

ናስሩዲን አህያው ላይ ተቀምጦ ሲሔድ የሚያውቀው የመንደሩ ሰው ያገኘዋል ።

«የት መሔድህ ነው ፣ ናስሩዲን ?»

«ወደ ከተማ ልወጣ ነው ።»

«እረ ፣ መንገዱ ከፍቷል ይባላል ! አህያህን እንዳይዘርፉህ ። ለመሆኑ እንዴት ባዶ እጅህን ከቤት ትወጣለህ ?»

ናስሩዲን መንገድ ከጀመረ በኋላ እንደገና ወደ ቤቱ መመለስ ያልፈለገ መሆኑን ሰውዬው ሲረዳ ፣ ራሱንና አህያውን መጠበቂያ እንዲሆነው ጐራዴውን ፈትቶ ያስታጥቀዋል ።

ናስሩዲን ጕዞውን ቀጥሎ አንድ ሠዋራና ጭር ያለ ስፍራ ሲደርስ ፣ አንድ ሰው ከሩቅ ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲመጣ ያያል ።

«ይኸ ወንበዴ መሆን አለበት ። ተጠንቅቄ ነው የምጠብቀው !» አለ ናስሩዲን — ለራሱ ።

ሰውዬው ቀረብ እያለ ሲመጣ ፣ ናስሩዲንን ፍርሐት ፍርሐት ይለው ጀመር ። በመጨረሻም ሰውዬው አጠገቡ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ፣ የታጠቀውን

ጕራዴ ፈትቶ ፣ «እባክህን ፣ ይህንን ጕራዴ ውሰድና እኔንና አህያዬን የዛሬን ማረን !» በማለት ልመናውን ያጕደጕደው ጀመር ።

በነገሩ የተደነቀው መንገደኛም ጕራዴውን ተቀብሎ መንገዱን ቀጠለ ።

ናስሩዲን ወደ ከተማ ሲመለስ ፣ ጕራዴውን ያዋ ሰው ሰውዬ መንገድ ላይ ጠብቆ እንዳገኘው ፣ «ታዲያስ ፣ ጕዞው እንዴት ነበር ?» በማለት ናስሩዲንን ቢጠይቀው ፦

«ጠዋት የነገርከኝ ነገር ሁሉ ትክክል ነው ። ያንተ ጕራዴ ባይኖር ኖሮ እኔና አህያዬ አልቆልን ነበር !» የሚል መልስ ሰጠው ።

— ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል ።

# አልምራችሁም ነበር

ናስሩዲን እቤቱ ተቀምጦ ነገር ያሰላስላል ። ለራሱ መልሶ መላልሶ ፣ «አንዳንድ ሰዎች ሞተው ያልሞቱ ይመስላሉ ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሳይሞቱ የሞቱ ይመስላሉ ። ስለዚህ ሰዎች መሞት አለመሞ ታቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል?» ይላል ።

የመጨረሻውን ዐረፍተ—ነገር በአፅንኦት ሲደ ጋግም የሰማችው ባለቤቱ ፣ «እዬ የኛ ፈላስፋ! ሰው መሞት አለመሞቱን ማወቅ አትችልም ማለት ነው? እኔ ልንገርህ ፤ አንድ ሰው እጁና እግሩ ቅዝቅዝ ካለ ሞቶአል ማለት ነው!» አለችው ።

ጥቂት ቀናት ቆየት ብሎ ናስሩዲን አህያውን ይዞ የማገዶ እንጨት ፍለጋ ወደ አንድ ራቅ ወዳለ ጫካ ሔደ ። እዚያ ግንድ መሳይ ጥሎ የማገዶ እንጨት ሲፈላልጥ ፣ በርድ በሰውነቱ ገብቶ ኖሮ እግርና እጁን ዠርምት አደረገው ። በዚህ ጊዜ ናስሩዲን ፣ «ይኸው እንግዲህ ፣ እጅና እግሬ በብርድ ተኰማትሮ ብረት ስለሆነ መሞቴ ነው ። የሞተ ሰው ደግሞ እንጨት መፍለጥ ቀርቶ ካለበት ቦታ ንቅንቅ አይልም» ይልና ከአንድ ዛፍ ሥር ሔዶ ይጋደማል ።

አህያውን በቋመጠ የተራበ ዓይን ይመለከቱ የነበሩ ቀበሮዎች ናስሩዲን የተኛ መስሎአቸው እንዴ ግልብጥ ብለው በመድረስ እንክት ያደርጉት ጀመር ።

ናስሩዲንም ዓይኑን አጨንቍሮ ያህያውን መበ ላት በመመልከት ፣ «መቼም በሕይወት እንቅስቃሴ ፣ ማንኛውም ነገር መንሥኤና ውጤት እንዳለው የታ ወቀ ነው ። ባልሞት ኖሮ አህያዬን እንዲህ አድርጋ ችሁ ስትዘነጣጥሉት እያየሁ አልምራችሁም ነበር!» አለ ።



## እኔ ማን ነኝ ?

ናስሩዲን በባግዳድ ከተማ በጉብኝት ላይ ሳለ ፣ የከተማዪቱ የሕዝብ ብዛት ፣ ግርግሩ ፣ ትርምሱ ፣ ውካታውና ጫጫታው አዕምሮውን አናወጠው ። ሁኔታው ከዚህ ቀደም አጋጥሞት ከሚያውቀው የተለየ ሆኖ በማግኘቱ ፣ ግራ ቀኝ ከሚተመው ሕዝብ ፈንጠር ብሎ በመቀመጥ ፣ «ይህን በመሰለ አዕምሮ በሚያዞር ታላቅ ከተማ ውስጥ ፣ ይኸ ሁሉ ሰው እሱ ነቱን ለመለየት እንዴት ይችላል?» እያለ ማሰብ ያዘ ። «በዚህ ቊጥር ስፍር በሌለው ሕዝብ መካከል ራሴን እንዳልዘነጋ መጠንቀቅ አለብኝ» አለ ናስሩ ዲን ፣ ሥጋት በተጫነው ስሜት ።

ናስሩዲን ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ አንድ እንግዶች ማረፊያ ሔደ ። እዚያም አልጋ ተከራይቶ ለማረፍ ወሰነ ። በተከራየው ክፍል ውስጥ ሁለት አል ጋዎች ነበሩበት ። አንደኛውን አልጋ ፣ አንድ ሰው ቀድሞ ተከራይቶት ኖሮ ፣ ናስሩዲን ሰውዬውን አል ጋው ጫፍ ተቀምጦ አገኘው ። ናስሩዲን ፣ ጋደም ብሎ ጥቂት ለማረፍ ፍላጐት ቢኖረውም ፣ ተኝቼ ስነቃ ድንገት ራሴን ብረሳስ የሚል ሥጋት አደረበት ። በመጨረሻም አብሮት ክፍሉን ለተከራየው ሰው የልቡን ገልጾ አዋየው ።

ሰውዬው ቀልደኛ ኖሮ ፣ ከኪሱ አንድ የልጆች መጫወቻ ፊኛ አውጥቶ በመንፋት ፣ «ነገሩ ቀላል ነው ። ይህንን ፊኛ አንዱ እግርህ ላይ አሥረህ ተኛ ። ስትነቃ ፣ ፊኛው እግሩ ላይ ታሥሮ የምታገኘው ሰው አንተ ነህ ማለት ነው!» አለው ።

«በጣም ጥሩ ዘዴ ነው!» አለ ናስሩዲን ፣ በነገሩ በመስማማት ።



ከሁለት ሰዓት መኝታ በኋላ ናስሩዲን ከእንቅልፉ ነቃ ። ቀና ብሎ ወዲህ ወዲያ ቢመለከት ፥ ፈኛው ስውዬው እግር ላይ ታሥሮ አገኘው ። «እዎን ፥ ያ ሰው እኔ ነኝ ማለት ነው!» አለ ናስሩዲን ። ወዲያውም በነገሩ ግራ በመጋባት ፥ ፍርሐት እያንቀ ጠቀጠው ፥ አጠገቡ የተኛውን ሰውዬ በቡጢ እየነ ረተ ፥ አንተ ሰው ተነሥ! ተነሥ ነው የምልህ! ያ የፈራሁት ነገር መድረሱ አልቀረም ።እባክህ ተነሥ!» በማለት ይጮህ ጀመር ።

ሰውዬውም ከእንቅልፉ በመነሣት ናስሩዲንን ምን ችግር እንዳጋጠመው ጠየቀው ። ናስሩዲንም ወደ ፈኛው አቅጣጫ በእጁ እየጠቆመ ፥ «የፈኛው ምል ክትነት ከታመነ አንተ እኔን ሆነሃል ። አንተ እኔን ከሆንክ—በፈጣሪ ይገቤሃለሁ— እኔ ማን ነኝ!» አለው።

## ዳሩ ምን ያደርጋል

አንድ ቀን ናስሩዲን ከተማሪው ጋር ወደ ገጠር ወጣ ብሎ ሲንሸራሸር ፥ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ውብ በሆነ አካባቢ የሚገኝ ሐይቅ አየ ። በአካባቢው የተፈጥሮ ውበት ለረጅም ጊዜ በተመስጦ ከቆየ በኋላ ፥ «ምን ዓይነት ውበት ነው! ምን ዓይነት ልምላሜ ነው!» ካለ በኋላ ፥ «ዳሩ ምን ያደርጋል!...» የሚለውን ሐረግ ሲደጋግም የሰማው ተማሪው ፥—

«መምህር ፥ ለምን 'ዳሩ ምን ያደርጋል' ትላለህ?' በማለት ጠየቀው ።

ናስሩዲንም ፥ «ያካባቢው ውበት ታይቶ አይጠ ገብም ። ዳሩ ምን ያደርጋል ፤ ውኃ መሐሉ ላይ ቸለ ሱበት!» አለው ።



# የዘመድ ዘመድ

የናስሩዲን የሥጋ ዘመዱ ከባላገር መጥቶ ቤቱ ውስጥ በእንግድነት ይሰነብታል ። ሰውዬው ካገር ቤት አንዲት ፈርጠም ያለች ዳክዬ ይዞለት መጥቶ ስለነበር ፣ ናስሩዲን ዘመዱ ያመጣለትን ስጦታ በደስታ ተቀብሎ ፣ ዳክዬዋም ታርዳ አብረው ሲበሉ ከሰነበቱ በኋላ ሰውዬው ወደ አገሩ ይመለሳል ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ አንድ ሌላ ሰው የናስሩዲን ዘመድ ከሚኖርበት መንደር ይመጣና በእንግድነት እንዲያሳድሩት በመጠየቅ ፣ «የዚያ ዳክዬ ይዞልህ የመጣው ዘመድህ ወዳጅ ነኝ» በማለት ለናስሩዲን ያስረዳል ። ናስሩዲንም ሰውዬውን ተቀብሎ በሚገባ አብልቶ ፣ አጠጥቶ ካሳደረው በኋላ በማግሥቱ ወደሚሔድበት ይሸኘዋል ።

በዚህ ዓይነት ገጠር የሚኖረውን የዘመዱን ስም የሚጠሩ ብዙ የባላገር መንገደኞች የናስሩዲንን ቤት በእንግድነት ያጨናንቁት ጀመር ።

አንድ ቀን አንድ ሰው ይመጣና ፣ «እኔ ከባላገር ዳክዬ ይዞልህ የመጣው ሰውዬ የወዳጁ ወዳጅ ነኝ!» ይለዋል— ናስሩዲንን ።

ናስሩዲንም በደስታ ተቀብሎ ቤቱ ያስገባውና ለሚስቱ አንድ ነገር በጆሮዋ ሹክ ይላታል ። እራት ቀርቦ እንግዳው ከሾርባው ሁለት ሦስት ጊዜ ከቀመሰ ለት በኋላ፣የሙቅ ውኃ እንጂ የሾርባ ጣዕም ስላጣበት፣ ወደ ናስሩዲን ዞር ብሎ ፣ «ለመሆኑ ይኸ ምን የሚሉት ሾርባ ነው ?» ብሎ ይጠይቃል ።

ናስሩዲንም ከሾርባው ቀመስ እያደረገ ፣ «ይኸማ ፣ ያኔ ከባላገር የመጣልኝ ዳክዬ የሾርባው ሾርባ ሾርባ ነው!» በማለት ይመልስለታል ።

— የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል ።

«በየዘመናቱ እንኳ ሰዎች ከግብረ[illegible]
ብነ ጥበብ [illegible] ብዙ የፍልስፍና እው[illegible]
ነመቅሰም ጥረት አድርገዋል። ዛሬ ቀልዶቹን [illegible]
ያነላ ማንኛውም ሰው — [illegible] በቀር — [illegible]
ጠቀሜታ ያላቸውን እንደሚያገኝባቸው ጥርጥር የለ[illegible]
ቀልዶችን ለጥሞና ለማንበብ ጊዜ [illegible] ያተርፋል[illegible]
ጸሐፊትን [illegible] ለማግኛዘብ [illegible]

ARTISTIC [illegible]

ዋጋ [illegible]